የኢትዮጵያ
ኢንተርፕራይዝ ልማት

# የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች

## የኢንቨስትመንት ማቋቋሚያና ማስፋፊያ ሰነድ

| አዘጋጆች | የሚሰሩበት ተቋም | ሚና |
|---|---|---|
| አቶ ሲራክ ማሞ ኃይለመለኮት | ከኢትዮጵያ ኢንርፕራይዝ ልማት | አስተባባሪ |
| አቶ ጺጋየ ቦንሳ | ከኢትዮጵያ ኢንርፕራይዝ ልማት | አባል |
| አቶ ግርማይ ገብረኪዳን | ከትግራይ ኢንዱስትሪ ቢሮ | አባል |
| አቶ ዳዊት አዱኛ | ከኢትዮጲያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | አባል |

**ሰኔ 2017 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## የዘርፉ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች

### I. ተልዕኮ

- ለዘርፍ ልማት ምቹ ሁኔታን  መፍጠር፤
- የዘርፉን አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት አቅም መገንባት፤
- መሠረተ ልማቶችን ማልማት፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር ማሳደግ፤
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍን ማስፋፋትና ተወዳዳሪ ማድረግ፤

### II. ራዕይ

"በ2022 በአፍሪካ የተወዳዳሪነት ተምሳሌት የሆነና በአገራችን ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ ያለው የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ዘርፍ ተገንብቶ ማየት!"

### III. እሴቶች

- ታታሪ፣ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሃብት ማፍራት፤
- ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ማስፈን፤
- ለቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መትጋት፤
- የተሳለጠ ቅንጅታዊ አሰራር ማስፈን፤
- አዳዲስ አሠራርና ፈጠራን ማበረታታት፤
- እድገት፣ ጥራትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማበረታታት፤
- አሳታፊነት፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤
- በሀገር ምርት መኩራት፤
- ተአማኒ፣ ተደራሽና ወቅታዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት፤
- ለማያቋርጥ ለውጥ ዝግጁ መሆን፤

*ማዉጫ* *ገጽ*

ክፍል አንድ ............................................................ 1
1.1 መግቢያ ............................................................ 1
1.2. የቃላት ትርጓሜ ............................................................ 2
1.3 ዓላማ ............................................................ 3
1.4 አስፈላጊነት ............................................................ 3
1.5 የተፈጻሚነት ወሰን ............................................................ 4
1.6 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ መርሆች ............................................................ 4
1.7 የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማልማት ያለዉ ፋይዳ ............................................................ 4
ክፍል ሁለት ............................................................ .6
2.1. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ............................................................ 6
2.2 በኢትዮጵያ የአነስተኛና መከካለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ ዳራ /BACKGROUND/ ............................................................ 7
2.2. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ነባራዊ ሁኔታ ............................................................ 9
2.3 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አስቻይ ሁኔታዎች ............................................................ 13
ክፍል ሦስት ............................................................ 15
3.የማኑፋክቸርንግ የኢንቨስትመንት አማራጮች ............................................................ 15
ክፍል አራት ............................................................ 22
4.በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱትሪዎች ያሉ መልካም አጋጣሚዎች ............................................................ 22
ክፍል አምስት ............................................................ 32
5. የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች እና ድጋፎች ............................................................ 32
5.1 ማበረታቻዎች ............................................................ 32
5.1.1 በኢንቨስትመንት ህጎች መሰረት የሚሰጡ ድጋፎች ........................................ ..... ...32
5.2. ድጋፎች ............................................................ 37
ክፍል ስድስት ............................................................ 42
6.ባለሀብት መሳብ ............................................................ 42
6.1 የኢንቨስትመንት ሂደት (The Investment Process) ............................................................ 42
6.2 በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ባለሀብቶች/ድርጅቶች ............................................................ 43
ክፍል ሰባት ............................................................ 45
7.የኢንቨስትመንት ማሳለጫ ስልቶች ............................................................ 45

ክፍል ስምንት........................................................................................................................47
8. የንግድ ድርጅት ምስረታ አይነቶች ..........................................................................................47
ማጣቀሻ (Reference).............................................................................................................51
አባሪ 1፡- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 የገቢ ግብር ማበረታቻ.........................52
አባሪ 2፡ ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ .....................1
ተሽከርካሪዎች መመሪያ ቁጥር 942/2015 ........................................................................................1
አባሪ ፫ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተኪ ምርቶች ዝርዝር ......................................5

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

በአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መስክ የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ፣ በማበረታታት፣የሀገር ዉስጥ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት መጠን እና የተሳትፎ መስክ በማስፋት እና ከዉጭ ባለሀብቶች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ የዕዉቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማፋጠን እና የኢንቨስትመንት ክልላዊ ስርጭትን ማሻሻል አስፈላጊ ነዉ፡፡
የሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እድገትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የሚወሰነው በአብዛኛው በማኑፋክቸሪንግ አንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ስኬት ላይ ነው፡፡ የሀገራችን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም ማሳደግ እና የምርት ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ ከዘርፉ የሚጠበቀውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማፋጠን አልተቻለም፡፡
የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው እድገቱን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ብዙ መልካም አጋጣሚዎች እና የመልማት አቅም ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም የባለፉት አመታት የውጪ ንግድ አፈፃፀም፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ እንዲቀላቀሉ ማድርግ፣ የክህሎት፣ ምርምር ውጤቶችን በማስተሳሰር፣ የተማረ የሰው ሃይል አቅርቦት እና የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ልምድና ስኬቶች ማሳደግ ተጠቃሽ የመልካም አጋጣሚዎች ናቸው፡፡
በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 526/2015 የተሰጠዉን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችል በስራ ላይ ያለውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሰነድ መፈተሽ እና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የአነስተኛና መ ካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም እስካለተሰጠው ድረስ በዚህ የድጋፍ ማዕቀፍ ሰነድ ፦

1.2.1. **“ኢንቨስትመንት”** ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት ገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱ የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነዉ፤

1.2.2. **“ባለሀብት”** ማለት ካፒታል ስራ ላይ ያዋለ የሀገር ዉስጥ ባለሀብት ነዉ፤

1.2.3. **“ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዝ”** ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም የሰዉ ኃይልን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለዉጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለዉ ምርት የማምረት ነዉ፤

1.2.4. **“አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ”** ማለት ከ11 እስከ 50 ቋሚ ሰራተኞች ከብር 600,001 እስከ 10,000,000 ብር (ስድስት መቶ ሺህ አንድ ብር እስከ አስር ሚሊዮን) ብር የሆነ አምራች ኢንተርፕራይዝ ነዉ፣ሆኖም ግን በሰው ሀይል እና በጠቅላላ ሀብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሀብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

1.2.5. **“መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ”** ማለት ከ51 እስከ 100 ቋሚ ሰራተኞች ከብር 10,000,001 እስከ ብር 90,000,000 (አስር ሚሊዮን አንድ ብር እስከ ዘጠና ሚሊዮን) ብር የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፣ሆኖም ግን በሰው ሀይል እና በጠቅላላ ሀብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሀብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

1.2.6. **“ሊዝ ፋይናንሲንግ ”** ማለት ልማት ባንክ እና የክልሎች ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክስዮን ማህበራት ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የካፒታል እቃዎችን ገዝተው በዱቤ ግዥ ስርዓት (Hire-purchase modality) በኪራይ የሚያቀርቡት አገልግሎት ማለት ነዉ፤

1.2.7. **“የገበያ ትስስር”** ማለት ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ዕድል ለመፍጠር ከግል፣ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ በዓለም አቀፍና ሀገር ውስጥ ከሚገኙ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በግብዓትና ምርት አቅርቦት (በግዢና ሽያጭ) በጎንዮሽና በተዋረድ ግንኙነት በህጋዊ የውል ስምምነት መሠረት የሚፈጠር የገበያና ግብይት ሥርዓት ነው፤

1.2.8. **"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ለሽያጭ የሚዉሉ ምርቶችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚዉል መሣሪያን እና እነዚህን የመሳሰሉ ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸዉን ሌሎች ንብረቶችን ይጨምራል፤

1.2.9. **"የጉምሩክ ቀረጥ"** ማለት በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጣሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን ይጨምራል፤

1.2.10. **"የገቢ ግብር "** ማለት የፌደራሉ መንግስት ወይም የክልል መንግስታት ወይም የሁለቱ የጋራ ገቢ የሆነ በትርፍ ላይ የሚጣል ታክስ ነው፤

## 1.3 ዓላማ

ባለሀብቶች በአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲሰማሩ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ስራ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት እንዲሁም በዘርፉ ተሰማርተዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በመንግስት የሚሰጡ ድጋፎችን ተደራሽ እንዲሆኑ በማስቻል፣ በቀጣይ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ኢንቨስትመንት ማስፋፋት፡ ፡

## 1.4 አስፈላጊነት

ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መንግስታዊ ድጋፎች በተለያዩ ተቋማት የሚሰጥ ቢሆንም ወጥ የሆነ ግንዛቤ ማስያዝ እና የድጋፍ አሰጣጥ ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት በዘርፉ የተሰማሩ እና መሰማራት ለሚፈልጉ የሀገር ዉስጥ ባለሀብቶች፣ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች፣ የዩኒቨርሲቲ እና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን፣ የፈጠራ ባለቤቶች እንዲሁም ዲያስፖራዎች መንግስት የሚሰጣቸዉን ድጋፎች ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር ያለዉን ክፍተት ለመሙላት ይህን ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 1.5 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ሰነድ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተሰማርተዉ ያሉ እንዲሁም ከሌሎች ዘርፎች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ መግባት ለሚፈልጉ የሀገር ዉስጥ ባለሀብቶች ፣ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች፣ የዩኒቨርሲቲ ፣ የቴክኒክና ሞያ ምሩቃን በውጪ ሀገር ያሉ ዲያስፖራዎች የሚያካትት ይሆናል፡፡

## 1.6 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ መርሆች

- የገበያ መር መርህ ይከተላል፤
- በጥራትና ዉድድር ላይ የተመሰረተ አሰራርን ይከተላል፤
- የግል ዘርፉ መሪ ተዋናይ ይሆናል፤
- የሀገር ዉስጥ ግብዓት በብዛት የሚጠቀም፣ እሴት የሚጨምር እና ሰፊ የስራ ዕድል የሚፈጥር አሰራር ይከተላል፤
- ለውጪ ገበያ ማቅረብና ከውጪ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ሚዛን በጠበቀ መልኩ ይመራል፤
- የሀገር ዉስጥ እና የዉጭ ሀገር ዜጎች በቅንጅት (Joint venture) እንዲሰሩ ያመቻቻል፤
- አካታችና ዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ይረጋገጣል፤

## 1.7 የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማልማት ያለዉ ፋይዳ

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ቅንጅታዊ አሰራሮችን የሚያጠናክር፣ የነባር አምራቾችን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል ጥራት ያላቸዉ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ለስራ ዕድል ፈጣራ አስተጽኦ እንዲያበረክት ፣ የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት ፣ በጥራትና በዓይነት ማምረት እና የሀገር ዉስጥ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ በስፋት እንዲሰማራ እና ትርፋማ እንዲሆኑ የሚያደርግ እንዲሁም ለጠቅላላ የሀገር ዉስጥ ምርት አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነዉ፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት፡-

- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዉን የማምረት አቅም አጠቃቀም የሚያሳድግ
- ስትራቴጂክ የሆኑ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ የማፋክቸሪንግ ኢንዱስትዎችን በማስፋፋት የሀገር ዉስጥ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶችን ጠቅላላ የሀገር ዉስጥ የገበያ ድርሻ የሚያሳድግ፤
- የምርት ጥራትን በማሻሻል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዉን ተወዳዳሪነት የሚያሳድግ፤
- ጥራት ያለዉ ኢንቨስትመንት በመሳብና ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ዉጤት በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ የሚያተኩር መሆኑ፤
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የሚያበረክት መሆኑ፤

## የኢንቨስትመንት ጠቀሜታ

| ተጠቃሚዎች | የኢንቨስትመንት ጠቀሜታ |
|---|---|
| ባለሀብት | • አዳዲስ የገበያ ዕድሎች መፈለግ<br>• በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ሀብቶችን ማግኘት<br>• ትርፍን ማግኘት<br>• ሀብትን መፍጠር<br>• ካፒታልን በንብረት ላይ በማስቀመጥ ኪሳራን ይቀንሳል |
| ህብረተሰብ | • የስራ ዕድል ፈጠራ<br>• የግል ገቢ ማመንጨት<br>• አዲስ የአሰራር ዘዴዎች እና ቴክኖሎጂዎችን መማር<br>• ለአለም አቀፍ የስራ ሁኔታዎች ቅርብ መሆን<br>• የገበያ ማረጋጋት |
| ኢኮኖሚዉ | • ገቢ ማመንጨት<br>• ሀገራዊ ሀብቶችን መጠቀም<br>• የማህበረሰብ እድገት<br>• ለምርምር እና ኢንዱስትሪላይዜሽን ዕድል መፍጠር<br>• የውጭ ምንዛሬ ማመንጨት<br>• የምርት ገበያ ማስፋት<br>• ተጨማሪ ካፒታል እንቅስቃሴ/ማስገባት |
| ኢንዱስትሪዉ | • ከሌሎቹ ዘርፎች ተጠቃሚ መሆን<br>• በሽርክና የመስራት ዕድል<br>• ቴክኖሎጂን ማላመድ እና የፈጠራ ችሎታን ማሻሻል<br>• የሰራተኛ ምርታማነት ማሳደግ<br>• የተያያዥ አገልግሎቶች ዕድል |

## ክፍል ሁለት


### 2.1. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

በዘመናዊው የኢንዱስትሪ አመሰራረት ታሪክ ከግብርና እና ከእጅ ሥራ ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ እና የማሽን ማምረቻ ኢኮኖሚ የበላይነት የመቀየር ሂደት የአንዱስትሪ አቢዮት ይባላል። እነዚህ የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ለውጦች አዳዲስ የስራ እና የህብረተሰብ አደረጃጀቶችን በመሠረታዊነት አስተዋውቀዋል ። ይህ ሂደት በብሪታንያ የጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን ከዚያም ወደ ሌሎች የአለም ክፍሎች እንደተዳረሰ ማስረጃዎች ያሳያሉ።

በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ  አዳዲስ የኢንዱስትሪዎች ቁጥራቸው እየጨመረ ከመምጣቱም በላይ ዘመናዊው ኢንዱስትሪ ጥቅም ላይ ያልዋሉትን በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ማለትም ቀለል ያሉ ብረቶችን፣አዳዲስ የኬሚካል ግኝቶችን ፣ እንደ ፕላስቲክ ያሉ ሰው ሰራሽ ምርቶችን እንዲሁም አዳዲስ የኃይል ምንጮችን መጠቀም ተጀመረ።

ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለሥራ ስምሪት ጠቃሚ ዘርፍ ከመሆናቸውም ባሻገር በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ በጣም ወሳኝ ሚና እንዳላቸው እየታወቀ መጣ። በአሁኑ ጊዜ በዓለም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በአማካይ 16% የሀገራዊ ምርት ድርሻ (GDP)፣ የማኑፋክቸሪንግ ዉጤቶች  የዓለም አቀፍ ንግድን 70%፣ የስራ ዕድል ፈጠራ ትልቅ ድርሻ (በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ከ30% በላይ የስራ ዕድል የሚፈጥር) ያለዉ ሲሆን በተጨማሪ የቴክኖሎጂ፣ አዳዲስ ፈጠራ፣ የጥናትና ምርምር፣ ሰዉ ሰራሽ አስተዉሎት (Artificial Intellegence) ስራዎች  በዘርፉ ዉስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸዉ። (ምንጭ፡- https://www.britannica.com/event/Industrial-Revolution)

**ግራፍ 1፡ የእስያ ሀገሮች የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከጠቅላላዉ የኢኮኖሚ ድርሻ**




**ምንጭ:-** United Nations Economic and Social Commission for Asia and the Pacific (UNESCAP), Published periodically various years.

## 2.2 በኢትዮጵያ የአነስተኛና መከካለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ ዳራ /BACKGROUND/

እ.ኤ.አ ከ1930 በፊት የኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የማምረት ተግባራት እንደ ሽመና፣ ሸክላ፣ አንጥረኛ እና የቆዳ ሥራ ባሉ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ዙሪያ ያተኮረ ነበር። ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፉ የኢንዱስትሪ አብዮት እና የውጭ የቴክኖሎጂ ዕድገት የተነጠለች ስለነበር መንገድ፣ ባቡር እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታ እጦት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መስፋፋት እና ማደግ ለበርካታ አመታት እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፤ ስለሆነም በሀገር ደረጃ ዘርፉን የሚደግፍ ተቋም በ1934 ዓ.ም የግርማዊት እቴጌ መነን እጅ ጥበብ ትምህርት ቤት በሚል ስያሜ ተመሰረተ፤ በ1969 ዓ.ም የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ዕደጥበባት ማስፋፊያ ድርጅት /አዕማድ/ ተብሎ እንደገና

ተቋቋመ፤በ1984 ዓ.ም የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችና ዕደጥበባት ልማት ማስፋፊያ ድርጅት /አዕልማድ/ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ድርጅታዊ አቋሙ በወቅቱ ለአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና በሚያመች መልኩ ተደራጅቶ እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ቆይቷል፤ በ1990 ዓ.ም እንደገና የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች ልማት ድርጅት /ፌጥአንሥልድ/ በሚል ስያሜ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 33/1990 እንዲቋቋም ተደረገ፤ በ2003 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 201/2003 ዓ.ም የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በሚል ስያሜ ተቋቁሟል፤

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትግበራ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ እየተመዘገቡ የመጡ ለውጦች ለኢንዱስትሪው መሰረት መሆን በሚችሉበት ደረጃ መስፋት እንዲችሉ ቀደም ሲል በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ስር ይተገበር የነበረው የአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከመካከለኛው ማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ጋር አቀናጅቶ በልዩ ትኩረት ለመተግበር እንዲቻል በሚኒሰትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 373/2008 በአዲስ መልክ የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ በሚል ስያሜ እንዲቋቋም የተደረገ እና በ2014 ዓ.ም የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ መሰረት በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015 የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በሚል ስያሜ የተቋቋሞ ሁለት ሀገራዊ ዓላማዎችን ለማሳካት እየሰራ ይገኛል። እነዚህም ዓላማዎች፡-

I. ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ በማድረግ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት መደገፍና ለከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት መሠረት መጣል፤
II. አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን በማልማትና በማስተዳደር ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል፤


## 2.2. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት  ነባራዊ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ጉዞ በስርዓት ለውጥና በፖለቲካ አስተሳሰብ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተቀርጾ በልዩ የታሪክ ምዕራፍ ያለፈ ነው፡፡ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት (እ.እ.አ. 1930-1974) የኢንደስትሪ ልማት ጥረቱ የጀመረው ከውጭ በሚመጡ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶች በመታገዝ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በማምረት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የኢንዱስትሪ ዕድገት አዝጋሚ እና በአብዛኛው በከተማ ማዕከላት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የደርግ መንግስት (እ.እ.አ. 1974-1991) ወደ መንግስት መር የኢንዱስትሪ ሞዴል በመቀየር ኢንዱስትሪዎችን በመውረስና የመንግስት  በማድረግ ለትላልቅ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ትኩረት ሰጥቷል፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎች ራስን መቻልን ለማበረታታት የታለሙ ቢሆንም፣ ብቃት ማነስ እና አለማቀፋዊ መገለል የአምራች እድገት ገድቦት ኖሯዋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ መሰረት በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡

እ.ኤ.አ 1991 የተከሰተውን  የስርዓት ለውጥ ተከትሎ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የኢንዱስትሪ ልማትን ለማስፋፋት የልማታዊ መንግስት አካሄድን ያዘ፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና የኢትዮጵያን የአምራች ዘርፍ ልማት ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር ለማዋሃድ ያለመ የመሰረተ ልማት፣ የኢነርጂ እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ኢንቨስትመንቶች ዋና የመንግስት ስትራቴጂ ማዕከል ሆነዋል በማድረግ በስፋት ሰርቶዋል፡፡ እንደ ሐዋሳ እና መቀሌ ያሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መመስረት እንደ ጨርቃጨርቅ፣ አልባሳት እና አግሮ ፕሮሰሲንግ የመሳሰሉ ዘርፎችን በማስፋፋት ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቶዋለ፡፡ እነዚህ ፓርኮች የስራ እድል ፈጥረው 740 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ቢያመጡም፣ እንደ ድርጅቶች መዝጋት፣ ዝቅተኛ ዋጋ ባለው ምርት ላይ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ አለመሆነና አለመተማመን እና የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ያሉ ተግዳሮቶች ቀጣይነት ያለው እድገትን ላስመዝገብ እንደ ተግዳሮት የሚታዩ ናችው፡፡ (UNDP,2023 G.C)

በአሁኑ ወቅት መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊስ በማዘጋጀት በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ለማጠናከርና ለማስፋፋት የመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የኢንዱስት ክላስተር ልማት እና የፋይናንስ አቀአቅርቦት እና የአቅም ግንበታ ስራዎችን በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡


**ግራፍ 2: የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መሳብ (ከ2013- 2016 ዓ.ም)**




**ምንጭ:**ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር, 2016 ዓ.ም ሪፖርት

ከ2013 - 2016 ዓ.ም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አማካይ ዕድገት 8.03%፤ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 6.93% ድርሻ ያለው እና አማካይ የማምረት አቅም 53.55% ነዉ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ማኑፋክቸሪንግ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን 40.82% ብቻ የሚያረካ ሲሆን 59.8% ከውጭ የሚመጣ ነዉ (ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር, 2016 ዓ.ም ሪፖርት)።


**ግራፍ 3:** የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገት እና ከጠቅላላ የሀገር ዉስጥ ምርት ያለዉ ድርሻ




| | 2013 ዓ.ም | 2014 ዓ.ም | 2015 ዓ.ም | 2016 ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|
| የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገት (%) | 7.30% | 6.40% | 8.20% | 10.20% |
| ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ዉስጥ ምርት ያለዉ ድርሻ (%) | 6.80% | 6.80% | 6.90% | 7.20% |

**ምንጭ፡** ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር, 2016 ዓ.ም ሪፖርት

**ግራፍ 4፡** የአምራች ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ (ከ*2014— 2016 ዓ.ም)*





**ምንጭ፡** ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር, 2016 ዓ.ም ሪፖርት

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ የማምረት አቅም ከዓለም አቀፋዊ ደረጃ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ ሲሆን ዋና ዋና ተግዳሮቶች  አዳዲስ ቴክኖሎጂ እጥረት ፣ የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት ፣ በቂ መሠረተ ልማት አለመኖር ፣ የቢሮክራሲያዊ መሰናክሎች እና የገበያ ተደራሽነት ውስንነት ምክንያት ምርታማነታቸውን  ለማሳደግ ችግር ይገጥማቸዋል።

ሆኖም ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ አቅሟን ለማሻሻል እርምጃዎችን እየወሰደች ትገኛለች። መንግሥት ለኢንዱስትሪ ፓርኮችና ለመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች ለምሳሌ የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ልማት በጨርቃጨርቅና አልባሳት ምርት ላይ ትኩረት አድርጎ ለውጭ ገበያ ሲያቀርብ ቆይቷል። በተጨማሪም፣ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ ተደራሽነት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን እና የሀገር ውስጥ ባለሀብት  ለመሳብ የተሻሻሉ አስራሮች ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ፣ የሰው ሀይል ልማት በማካሄድ የዘርፉን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም  ምርትን ለማዘመንና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

**ግራፍ 5፡** የአምራች  ኢንዱስትሪ አማካይ የማምረት  አቅም  (2013 — 2016 ዓ.ም)




**ምንጭ፡** ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር, 2016 ዓ.ም ሪፖርት

## 2.3 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አስቻይ ሁኔታዎች

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ላይ የምትገኝ ሀገር ስትሆን፣ ሙሉ በሙሉ በሞቃታማ ኬክሮስ ውስጥ ትገኛለች፣ የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት 1,140,331 ካሬ ኪ.ሜ ሲሆን ከጠቅላላው የመሬት ስፋት ውስጥ 45% ለእርሻ ተስማሚ እና ብዙ ሊታረስ እና ሊለማ የሚችል መሬት ሲሆን ከዚህም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው 23% ብቻ ነው። የአገሪቱ ከፍታ ከባህር ጠለል በላይ 4,600ሜ, ከባህር ጠለል በታች 120 ሜትር ሲሆን ከ3 -15º N ኬክሮስ እና 33-48ºE ኬንትሮስ ላይ ትገኛለች።
ሀገራችን ለመካከለኛ ምስራቅ፣ ለኤስያና ለአውሮፓ ሀገሮች በቅርብ ርቀት የምትገኝ በመሆኑ በወደብ የወጪ ንግድም ማካሄድ ያስችላታል።
ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣት የኢትዮጵያ መንግስት ለዜጎቹ ከፍተኛ የትምህርት እድል በስፋት ይሰጣል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የዩኒቨርስቲዎች እ.ኤ.አ. 2022 መረጃ መሰረት ከአገሪቱ በጀት ከ35% በላይ የሚሆነው ለትምህርት ይውላል። 25% ያህሉ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን 46% የሚሆነው ህዝብ ማንበብና መጻፍ የሚችል ነው። 42 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ 83 የግል ዩኒቨርሲቲዎች እና ከ35 በላይ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይገኛሉ። የሀገሪቱ የመንግስት መዋቅር 12 ክልላዊ መንግስታት እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች ያሉት ፌዴራላዊ ስርዓት ነው። ሁሉም የክልል መንግስታት የራሳቸውን የልማት አላማ ለመወሰን የራሳቸው የአስተዳደር መዋቅር እና የራስ ገዝ አስተዳደር አላቸው።
እ.ኤ.አ. በ2023 አጠቃላይ የሀገሪቱ የህዝብ ብዛት ወደ 126,527,060 አካባቢ ሲሆን ከ15 - 64 ዓመት ዕድሜ ያላቸዉ 57.7 በመቶ ናቸዉ። ከ23.2% በላይ የሚሆነው ህዝብ በከተማ የሚኖር ነው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የከተሞች እድገት ካላቸው አምስት የአፍሪካ ሀገራት ተርታ ትሰለፋለች። እ.ኤ.አ. በ2030 አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር ከ143 ሚሊዮን በላይ እና የከተማው ህዝብ ከ34.6 ሚሊዮን በላይ ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ይህም ከተገመተው የህዝብ ቁጥር 24% ነው።
ይህም የከተማነት መስፋፋት እና በከተማ የሚኖረው የህዝብ ቁጥር መጨመር ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው መስፋፋት ከፍተኛ የሆነ በጎ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል። የቅርብ ጊዜ የስራ አጥነት መጠን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ አገልግሎት (ESS) መረጃ እ.ኤ.አ.2022 መሰረት የከተማ ስራ አጥነት መጠን 19.4% ነበር።

መንግሥት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት በግል ዘርፉ የሚመራ እና የሚያበረታታ አሠራር ዘርግቷል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር አዋጅ የፓርኮች ልማት በመንግሥትና በግል ዘርፉ እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፡፡

የሀገር ውስጥ አምራቾችን መደገፍና ማበረታታት ሀገራት ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የቴክኖሎጂ ሽግግር (ቴክኒካዊ፣ የገበያ፣ የኢንዱስትሪ አመራር፣ የኢንዱስትሪ የስራ ባህል፣ ወዘተ) ዕውቀትና ክህሎት ማስቀረት የሚችል አቅም በመፍጠር የአምራች ኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ሽግግር ማሳለጥ ያስችላል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ከባቢ ቀልጣፋና ግልፅ እንዲሆን በማድረግ የግል ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## 3. የማኑፋክቸርንግ የኢንቨስትመንት አማራጮች

### 3.1 ጨርቃጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ንኡስ ዘርፍ

የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት በስሩ የተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ መካካል የፈትል፣የሽመና እና ሹራብ ስራ፣ የማቅለምና ማተም ሲኖሩት እንዲሁም የአልባሳት ሥራ ዋነኛዎቹ ናቸው:: የዚህ ዘርፍ ውጤቶች በዓለም ባሉ ሀገራት በተለያዩ የቴክኖሎጂ ደረጃዎች እየተመረቱ ለየሀገራቱና ለዓለም አቀፍ ገበያ እየቀረቡ ይገኛሉ::

ኢትዮጵያ ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በዋናነት ግብአት የሚያገለግለው ጥጥ የምታመርትና ለጥጥ ልማት አመቺ የሆነ 3 ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬትና ተስማሚ የአየር ንብረት ያላት በመሆኑ ለዘርፉ ምቹ እንድትሆን አድርጎታል፡፡ እንዲሁም ሌሎች የግብአት ምንጮች የሆኑ የቃጫ ተክል ፤የተልባ ተክል፤ ሐር፤ ቀርከሀ፤ የመሳሰሉት ለማምረት ስፊና ምቹ የሆነች ሀገር ናት፡፡
ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት ባላቸው ተወዳዳሪነት የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የተሰጣቸዉ ምርቶች (በአባር 3 ተዘርዝሯል)፡፡ በተጨማሪም በንግድ ህጉ መሰረት የኢንቨስትመንት ፍቃድ የሚሰጥባቸዉ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንኡስ ዘርፍ ስር የሚመረቱ ምርቶች እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

### *ሀ/ ጨርቃጨርቅ ማምረት* (Textile)

- ጭረቶችን ማዘጋጀት፣መፍተል፣መሸመን፣ማጠናቀቅ እና/ ወይም ማተም (አልባሳትን ሳይጨምር)፤
- ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ድርና ማግ፣አልባሳትና ሌሎች የጨርቃጨርቅ ዉጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተር፣ በማፍካት፣ በማጠናከር፣ወርድና ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ፤
- ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆችን ወይም ሹራብ ወይም ምንጣፍ ማምረት፤

- የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት፤

**ለ/ አልባሳት ማምረት (Garment)**

- የጨርቃጨርቅ አልባሳትን ማምረት፣ የሹራብ ሥራ፣ፎጣ ማምረት፣ የጥልፍ ሥራ ብርድልብስ ፣ የተዘጋጁ የማስዋቢያና የጨርቃጨርቅ ቁሳቁሶች ማምረት

**3.2 ምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ንኡስ ዘርፍ**

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የብሄራዊ የአምራች ዘርፍ ተኪ ምርት ስትራቴጂ (2016 ዓ.ም) ላይ እንደተገለጸዉ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት ባላቸው ተወዳዳሪነት 11 የምግብ እና የመጠጥ ምርቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነሱም የቢራ ብቅል፣ ፓስታና ማካሮኒ፣ ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ ማንጎ ጁስ፣ የምግብ ዝግጅት፣ የበቆሎ ውጤቶችና ስናክስ፣ የዳቦ መጋገሪያ ምርቶች፣ ልዩ ልዩ የዱቄት እይነቶች፣ የእንስሳት ውጤቶች እና የበለፀጉ ምግቦችን (አልሚ ምግቦች) ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አቅም አለው፡፡ በተጨማሪም በንግድ ህጉ መሰረት የኢንቨስትመነት ፍቃድ የሚሰጥባቸዉ የምግብ እና መጠጥ ንኡስ ዘርፍ እንደሚከተለዉ ተዘርዝረዋል፡፡

**ሀ/የምግብ ኢንዱስትሪ**

- ሥጋና የሥጋ ዉጤቶች ማቀነባበር፣ ዓሳና የዓሳ ዉጤቶችን ማቀነባበር፣ አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበር
- የምግብ ዘይት ማምረት
- ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ዉጤቶችን ማምረት
- የምግብ ማሻሻያ፣ ተጨማሪዎች ወይም ንጥረ ነገሮች ወይም ስታርችና የስታርች ዉጤቶች ማምረት
- የእህል ምርት ዉጤቶችን ማቀነባበር (ዱቄት ማምረትን ሳይጨምር)
- ስኳር ማምረት
- ማካሮኒ፣ ፓስታ እና /ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት

- አዮድን የተጨመረበት ጨዉ ማምረት
- ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት
- የእንስሳት መኖ ማቀነባበር፣ የኦቾሎኒ ቅቤ ማምረት፣ማር እና ሰም ማቀነባበር፣ ጥራጥሬ የቅባት እህል ማቀነባበር
- የቅመማ ቅመም ማቀነባበሪያ፣ ዱቄት ማምረት

**ለ/ የመጠጥ ኢንዱስትሪ**

- የአልኮል መጠጥ ማምረት፣የወይን ጠጅ ማምረት፣ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት
- የማዕድን ወይም የታሸጉ ለሎች ዉሃዎችን ማምረት፣ለስላሳ መጠጥ ማምረት

### 3.3 ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ

መንግስት ትኩረት ከሰጣቸው ዘርፎች መካከል የቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አንዱ ሲሆን እሴት በመጨመር ፤የስራ ዕድል በመፍጠር፤ ኤክስፖረት በማድረግ እና ገቢ ምርት በመተካት ሀገሪቱ አጠቃላይ ምርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ዘርፍ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በእንስሳ ሀብቷ ወደ 42.9 ሚሊዮን በጎች፤ 52.6 ሚሊዮን ፍየሎች እና 71.8 ሚሊዮን ከብቶች ያላት በመሆኑ በቂ ግብዓት በሀገር ውስጥ ይገኛል፡፡በዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንተርፕራይዞች በሚያመርቱት ምርት ብቻ የሀገር ውስጥ የገበያ ፍላጎትን ማሟላት ባለቻሉ በዓመት እስከ 121 ሚሊየን ዶላር የሚያወጣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርት ከውጭ ሀገር ታስገባለች፡፡ ይህን የገበያ ክፍተት ለመሙላት መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በንግድ ህጉ መሰረት የኢንቨስትመንት ፍቃድ የሚሰጥባቸው ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንኡስ ዘርፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ (ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋትን አይጨምርም)
- ካለቀበት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት
- የቆዳ ዉጤቶች እና/ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት
- የቆዳ ጫማ ማምረት
- የቆዳ ልብሶች ፣ የጉዞ ዕቃዎች ፣ የሴቶች የእጅ ቦርሳ ፣ ቦርሳዎች ፣ ኮርቻ እና ልጉዋም ሌሎች አጠቃላይና አነስተኛ የቆዳ ውጤቶች ማምረት

## 3.4 ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ዉጤቶች ኢንዱስትሪ

የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ኢንዱስተሪ ንዑስ ዘርፍ በአብዛኛዉ ከዉጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት አገራችን የምታወጣዉን የዉጭ ምንዛሬ በማስቀረት የንግድ ሚዛኑን ለማስተካከል የሚረዳ ዘርፍ ነዉ፡፡ በዚህ ዘርፍ በሀገር ውስጥ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች አምራች ኢንተርፐራይዞች በሚያመርቱት ምርት ብቻ የሀገር ውስጥ የገበያ ፍላጎትን ማሟላት ባለቻሉ በአመት እስከ 2.3 ቢሊየን ዶላር የሚያወጣ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ምርት ከውጭ ሀገር ታስገባለች ፡፡ ይህን የገበያ ክፍተት ለመሙላት መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ በመሆኑ ዜጎች በንግድ ህጉ መሰረት የኢንቨስትመንት ፍቃድ የሚሰጥባቸው የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንኡስ ዘርፍ እንደሚክተለው ቀርቧል፡፡

- መሰረታዊ ኬሚካሎችን (ኢታኖልን እና /ወይም ሰዉ ሰራሽ ጭረቶችን ጨምሮ)፣ እና/ወይም ሃይድሮጂን እና አሞኒያ ማምረት
- ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትጂን ዉህዶችን ማምረት
- መሰረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) ፕላስትኮችን እና/ወይም ሲንቴቲክ (ሰዉ ሰራሽ) ጎማ ጥሬ ዕቃዎችንና ጎማ ዉጤቶችን ማምረት
- ጸረ-ተባይና ግብርና ኬሚካሎችን ማምረት
- የግድግዳ ቀለም፣ ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች፣ ማጣበቂያ እና/ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ኬምካሎችን ማምረት
- የንፅህናና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች (ሽቶ፣የውበት እቃዎች ለሽቶ የሚያገለግሉ ኬሚካሎች የመዓዛማ ዘይቶችና ሬዚኖይድስ ማምረት) እና ግብዓቶች መፈብረክ
- ሰዉ ሰራሽ ጭረቶችን ማምረት
- ማርብልና እና ግራናይት ማምት፣ የሴራሚክስ ማምረቻ ፤ቴራዞ ማምረቻ ፤ኮንክሪት ፖል ማምረቻ፤ባዞላ ማምረቻ እና ሌሎች የግንባታ ዕቃዎች ማምረት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ፡፡

## 3.5 የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ውጤቶች

የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ አምራች ኢንተርፕራይዞች ንኡስ ዘርፍ በመንግስት ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ሲሆን በአብዛኛው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ሀገራችን የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ በማስቀረት የንግድ ሚዛኑን ለማስተካከል የሚረዳ ዘርፍ ነው፡፡በዚህ ዘርፍ በሀገር ውስጥ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ አምራች ኢንተርፕራይዞች በሚያመርቱት ምርት ብቻ የሀገር ውስጥ የገበያ

ፍላጎትን ማሟላት ባለቻሉ በዓመት እስከ 4 ቢሊየን ዶላር የሚያወጣ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ምርት ከውጭ ሀገር ታስገባለች። ይህን የገበያ ክፍተት ለመሙላት መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ በመሆኑ ዜጎች በንግድ ህጉ መሰረት በኢንቨስትመንት የሚሳተፉባቸው የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንኡስ ዘርፍ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ከብረት እና ማግኔተዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ/ማድለብና የተለያዩ ቅርጾችን መፈብረክ
- የማዋቀሪያ እና የተለያዩ የብረታ ብረት ዉጤቶችን ማምረት
- በርና መስኮት ሥራዎች ፣ቀላል ማሽነሪዎችን ማምረት
- ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ማምረት፣የማሽነሪ መለዋወጫዎች

## 3.6 መስታወት እና የመስታወት ውጤቶች

- የመስታወት መያዣዎችን፣ ከመስታወት የሚመረቱ የማዕድ ቤትና የገበታ እቃዎች ማምረት
- ሌሎች ሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ሌሎች መስታወት እና የመስታወት ውጤቶች ማምረት

## 3.7 የከበሩ ማዕድናት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረት ውጤቶች

- የከበሩ ማዕድናት ማንጠር ወርቅ፣ ብር፣ ፕላቲኒየም የመሳሰሉትን ማምረት
- ከከበሩ ማዕድናት ውጭ ለግብዓትነት የሚያገለግሉ ማግኔታዊ ያልሆኑ (አልሙኒየም፣ ዚንክ፣ሊድ፣ቲታኒየም ፣ኒኬል፣ነሓስ የመሳሰሉት) የብረታ ብረቶችን ውጤቶችን ማምረት
- ሌሎች ሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ የከበሩ ማዕድናት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶችን ማምረት

## 3.8 የእንጨት ዉጤቶች ኢንዱስትሪ

- የእንጨት ዉጤቶችን ማምረት
- እንጨት መሰንጠቅና ማለስለስ በአግባቡ መያዝና ማምረት
- የእንጨት ተረፈ ምረቶች ቡሽ ፣ ገለባ እና የመሳሰሉት ማምረት
- ሌሎች እንጨት መሰንጠቅና ማለስለስ የእንጨት ተረፈ ምርቶች ማምረት

- ኮምፔንሳቶ፣ ንብብር ጣውላ፣ ላሚን ቦርድ፣ ፓርቲክል ቦርድ፣ ሌሎች ፓናሎችና ቦርዶች ማምረት

## 3.9 የዕደ ጥበብ ዉጤቶችና ጌጣጌጥ ማምረቻ

- የከበሩ ድንጋዮች ማስጌጥ ሥራ፣የነሐስ ጌጣጌጥ ሥራ፣የአሸንጉሊት ስራ፣ የሙካሽ ሥራ

## 3.10 የግንባታ ግብዓት ምርቶችን ማምረት

- ቴራዞ ማምረት፣ ኮንክሪት ፖል ማምረት፤ባዞላ ማምረት፤ ጅብሰም ማምረት፣የግንባታ ዕቃዎች ማምረት
- ለህንጻ ግንባታ፣ለተሽከርካሪ ወይም ለሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶች ግብዓት የሚሆኑ ፣ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ ማስተላለፊያነት እንዲሁም ለፍሳሽ መስወገጃ የሚያገለግሉ የፕላስቲክ ቧንቧዎች ወይም መገጣጠሚያዎችን ማምረት

## 3.11 ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ

- መስታወት እና/ወይም የመስታወት ወይም የሴራሚክ ዉጤቶችን ማምረት
- የሸክላና የሲሚንቶ ዉጤቶች ማምረት
- የድንጋይ ዉጤቶችን፣ ዕብነ በረድ እና ግራናይት የኖራ ድንጋይ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርጽ ማውጣት እና ማጠናቀቅ
- ኖራ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን መምረት
- የወፍጮድንጋይ፣ የብርጭቆ ወረቀት ወይም መገደቢያ ወይም የሙቀት መከላከያ ምርቶችን ማምረት

## 3.12 ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሳሪያዎችን ማምረት

- መኪና አካላትን፣ ተጎታችን እና/ወይም ከፊል ተጎታችን ወይም መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት
- ጋሪዎችን ማምረት
- የሞተር ብስክሌቶችን፣ ብስክሌቶችን እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት

- የሞተር ብስክሌቶችን፣ ብስክሌቶችን እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ
- ጀልባዎችን መገንባት

## 3.13 ወረቀትና የወረቀት ዉጤቶችን መፈብረክ

- ፐልፐ እና /ወይም ወረቀት ማምረት፣የወረቀት ዉጤቶችን ማምረት

## 3.14 የፐላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ

- ፊስታልን ሳይጨምር የፐላስቲክ ውጠቶችን ማምረት

## 3.15 የማተሚያ ኢንዱስትሪ

- ለማስታወቂያ እና ለህትመት ሥራዎች የሚያገለግሉ እቃዎች እና ቀለሞች ማምረት

## 3.16 የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ

በሀገራችን መድኃኒት አምራች ፋብሪካዎች ትንሽ በመሆናቸው ምክንያት አብዛኛው ምክንያት አብዛኛው መድኃኒት ከውጭ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም አቅምና እውቀት ያላቸው ባለሀብቶች በዘርፉ ተሰማርተው መድኃኒቶችን በአገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚመጣውን በመተካት ራሳቸውንም ሆነ አገራቸውን እንዲጠቅሙ መንግስት ያበረታታል፡፡ ዘርፉ

- ለመድኃኒት ግብዓቶች የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃንት ዉጤቶች ማምረት
- ለሰው አገልግሎት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ)
- ለእንሰሳት አገልግሎት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ)
- ከመድኃኒት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን የማሸጊያ ምርቶችን ማምረት፡፡
- የመድኃኒት ማሸግ ሥራዎች

## ክፍል አራት

### 4. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱትሪዎች ያሉ መልካም አጋጣሚዎች

የማኑፋክችሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማሳለጥ እና ሀገሪቱን ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማብቃት መንግስት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ያደረገ ሲሆን ይህም እ.ኤ.አ 2015 በአለም አቀፍ ደረጃ ሶስተኛ ትልቅ ኢንቨስትመንት እንዲሁም ከሰሃራ በታች ከሚገኙ አፍሪካ አገራት አማካይ በሶስት እጥፍ የላቀ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ:: የመዋዕለ ንዋይ ፍሰቱ ዋና ትኩረት የነበረው የመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ ሲሆን እነዚህም በኃይል፣ በትራንስፖርት እና በሎጂስቲክስ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ሼዶች፣ በትምህርትና በጤና አጠባበቅን ያካትታል:: በዚህም በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ እድገትን ለማፋጠን በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የሰው ኃይል አቅርቦት፣ ሀገሪቱ 90 በመቶ የሚሆነውን የሃይል ፍላጎት ከታዳሽ ሀብቶች ማመንጨት፣ የተሳለጠ የአየር መንገድ አገልግሎት እንዲሁም የመንገድ፣ የባቡር እና የደረቅ ወደብ አገልግሎት ማስፋፋት እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደ ስራ ማስገባት አስችሏል::

የሀገራዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ትግበራም ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር ተጨማሪ እድል ይዟል:: በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ገበያን መሰረት ያደረገ አቅርቦትን በማስፋት እና ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ማሳደግ እና በሂደት የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚውን ወደሚመራበት ደረጃ ማድረስ ትኩረት አድርጎ የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው::

በዚሁ መሰረት የሀገር ዉስጥ ባለሀብቶች በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ያላቸዉን መዋዕለነዋይ ኢንቨስት በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያሉ ሀገራዊ መልካም አጋጣሚዎች፡-

### 4.1. መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት

- ተነጻጻሪ እና ተወዳዳሪ ምቹ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መቀረፁ፤
- ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር የሚደረግ ጥረት መኖር፤
- የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም እቅድ መኖር፤
- የ10 አመት የልማት እቅድ መኖር፤

- የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መጀመሩ፤
- የተለያዩ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችና የድጋፍ ማዕቀፎች መቀረፃቸው፤

## 4.2. አስተማማኝ የሆነ የግብርና ምርት

❖ ሀገራችን በአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስት ለማድረግ በእንስሳት ሀብቷ ከዓለም 10ኛ ከአፍሪካ 1ኛ ስለሆነች በቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ሥጋና ሥጋ ዉጤቶች፣ ወተትና ወተት ተዋጽኦ ማምረት ስራዎች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የጥሬ እቃ ችግር የሌለባት አገር ናት፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የአግሮ ኢኮሎጂካል ዞኖች (ቆላ፣ ወይናደጋ እና ደጋ) በመኖራቸው የተለያዩ የሰብል ምርቶች፣ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የደንዉጤቶች እንዲሁም የተለያዩ ካሽ ክሮፕ ለማምረት መሆኗ ምቹ ያደርጋታል፤

❖ በቆላውም ሆነ በደጋው በርካታ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ የተሰሩ ሃይቆች፣ ወንዞችና፣ ግድቦች ዉስጥ በርካታ የሚበሉ የአሳ ዝርያዎች መኖራቸዉ፤


❖ ከፍተኛ የስንዴ ምርት ያላትና እና ከአፍርካ ሶስተኛ የበቆሎ አምራች ሀገር መሆኗ፤

**ሰንጠረዥ 1. ሠንጠረዥ 2:** በሀገር ደረጃ ያሉ የቀንድ ከብት፣ በግ እና ፍየል ብዛት

| ክልል | የቀንድከብት | በግ | ፍየል |
|---|---|---|---|
| ትግራይ | 4,908,964 | 2,097,619 | 4,838,969 |
| አፋር | 1,959,185 | 4,476,485 | 8,843,082 |
| አማራ | 17,262,804 | 10,391,582 | 7,045,305 |
| ኦሮሚያ | 25,506,409 | 9,752,385 | 8,425,727 |
| ሶማሌ | 6,034,887 | 11,013,491 | 16,464,505 |
| ቤ/ጉ | 592,228 | 61,335 | 446,323 |
| ደቡብ | 11,128,017 | 4,561,504 | 5,518,806 |
| ሲዳማ | 2,413,482 | 467,858 | 308,903 |
| ጋምቤላ | 321,722 | 27,789 | 135,494 |
| ሀረር | 86,056 | 5,497 | 110,499 |
| ድሬዳዋ | 78,022 | 59,320 | 325,922 |
| **ድምር** | **70,291,776** | **42,914,865** | **52,463,535** |


ምንጭ :- "ESS 2021/2022 G.C“

**ግራፍ 6:** በሀገር ደረጃ ያሉ የዶሮ እና ግመል ብዛት





- ምንጭ :- "ESS 2021/2022 G.C"

**ግራፍ 7: በሀገር ደረጃ ያለ የንብ ቀፎ ብዛት**




ምንጭ :- "ESS 2021/2022 G.C "

**ግራፍ 8: የኢትዮጵያ የዉሃ አካላት እና የዓሳ ምርት ዕምቅ አቅም**




ምንጭ: Internatinal Journal of Fisheries and Aquatic studies, 2020 G.C

**ሠንጠረዥ 2: አመታዊ የቅባት እህሎች ምርት**

| የቅባት እህሎች | አጠቃላይ የእርሻ መሬት (በሄክታር) | | | አጠቃላይ የእርሻ መሬት (በሄክታር) | ጠቅላላ ምርት በኩንታል | | | አጠቃላይ ምርት (በኩንታል) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በልግ | መኸር | ትላልቅ የእርሻ መሬት /Large Scale Farmfarm) | | በልግ | መኸር | ትላልቅ የእርሻ መሬት /Large Scale Farmfarm) | |
| **የቅባት እህሎች** | 11,189 | 766,167.7 | 286,522.8 | 1,063,879.44 | 44,074.4 | 7,774,444.17 | 2,432,954.5 | 10,251,473.13 |
| ሰሊጥ | 4,749.30 | 369,897.3 | 280,330.1 | 654,976.74 | 5,423.03 | 2,602,576.33 | 2,331,185.7 | 4,939,185.09 |
| ኑግ | 67.04 | 191,766 | 527.60 | 192,360.64 | - | 2,147,979.02 | 5,352.96 | 2,153,331.98 |
| ኦቾሎኒ | 5,296.55 | 113,514.9 | 1,299.10 | 120,110.60 | 37,288.5 | 2,050,686.50 | 16,160.24 | 2,104,135.25 |
| ተልባ | 331.56 | 78,921.37 | 335.34 | 79,588.27 | 344.65 | 804,566.42 | 7,407.09 | 812,318.16 |
| ሰናፍጭ | 681.45 | 7,917.47 | 3,696.34 | 12,295.26 | 68.47 | 125,757.89 | 64,889.43 | 190,715.79 |
| ሱፍ | 63.14 | 4,150.55 | 334.25 | 4,547.94 | 949.76 | 42,878.01 | 7,959.10 | 51,786.87 |

ምንጭ : CSA 2021 **እ.ኤ.አ**

**ሠንጠረዥ 3: አመታዊ የጥራጥሬ ምርት**

| የእህል አይነት | አጠቃላይ የእርሻ መሬት (በሄክታር) | | | አጠቃላይ የእርሻ መሬት (በሄክታር) | ጠቅላላ ምርትር በኩንታል | | | አጠቃላይ ምርት (በኩንታል) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በልግ | መኸር | ትላልቅ የእርሻ መሬት /Large Scale Farm) | | በልግ | መኸር | ትላልቅ የእርሻ መሬት/Large Scale Farm) | |
| **ጥራጥሬ** | **401,363** | **1,674,950** | **58,647** | **2,134,959.7** | **2,581,034.6** | **31,999,988.7** | **1,280,916** | **35,861,938.6** |
| ባቄላ | 6,559 | 504,567 | 780 | 511,908.39 | 55,209.11 | 10,706,365.4 | 21,051.3 | 10,782,625.8 |
| አተር | 30,825 | 219,928 | 126 | 250,877.90 | 204,146.04 | 3,762,368.8 | 3,746.5 | 3,970,261.4 |
| ነጭ ቦለቄ | 24,571 | 103,289 | 8,898 | 136,757.46 | 178,111.36 | 1,855,340.7 | 227,343.4 | 2,260,795.5 |
| ቀይ ቦለቄ | 231,716 | 208,295 | 4,273 | 444,284.06 | 1,703,982.38 | 3,670,300.1 | 2,323.9 | 5,376,606.4 |
| ሽምብራ | 4,196 | 177,547 | - | 181,742.96 | 15,360.19 | 3,740,361.9 | - | 3,755,722.1 |
| ነጭ ሽምበራ | 3,951 | 43,172 | 8,274 | 55,397.52 | - | 832,831.8 | 133,613.6 | 966,445.4 |
| ምስር | 13,009 | 84,512 | 1.30 | 97,522.08 | 67,194.29 | 1,130,178.8 | 21.5 | 1,197,394.6 |
| ጉያ | 4,612 | 143,894 | 13.92 | 148,519.96 | 13,260.10 | 2,899,174.8 | 247.2 | 2,912,682.0 |
| አኩሪ አተር | 122 | 83,797 | 24,869 | 108,787.99 | - | 2,086,763.9 | 624,024.1 | 2,710,787.9 |
| አብሽ | 717 | 42,344 | 3.90 | 43,065.33 | 5,168.55 | 507,472.4 | 38.80 | 512,679.7 |
| ማሾ | 81,084 | 48,022 | 11,409 | 140,515.02 | 338,602.58 | 515,686.6 | 268,505.1 | 1,122,794.2 |
| ግብጦ | - | 15,580.99 | - | 15,580.99 | - | 293,143.6 | - | 293,143.6 |


ምንጭ፡ CSA 2021 እ.ኤ.አ

**ሠንጠረዥ 4**: አትክልቶች እና ፍራፍሬ ምርቶች በኢትዮጵያ

| የምርት ዓይነት | ጠቅላላ ምርትር /በኩንታል/ | የምርት ዓይነት | ጠቅላላ ምርት /በኩንታል/ | የምርት ዓይነት | ጠቅላላ ምርት /በኩንታል/ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አትክልቶች** | **8,767,991** | **ስራስር** | **50,989,511** | **ቋሚ ተክሎች** | **8,355,987** |
| ሰላጣ | 3,8230 | ቀይስር | 272,321 | አቮካዶ | 1,044,919 |
| ጥቅል ጎመን | 245,651 | ካሮት | 182,254 | ሙዝ | 5,390,277 |
| ጎመን | 4,358,626 | ሽንኩርት | 2,754,783 | ዘይቱን | 35,679 |
| ቲማቲም | 350,019 | ድንች | 9,245,284 | ሎሚ | 79,524 |
| ቃሪያ | 672,088 | ቦይና | 4,922,731 | ማንጎ | 1,051,874 |
| በርበሬ | 3,131,154 | ነጭ ሽንኩርት | 1,525,946 | ብርቱካን | 224,134 |
| ቆስጣ | 6,623 | ጎደሬ | 14,527,645 | ፓፓዬ | 517,941 |
| | | ስኳር ድንች | 17,558,548 | አናናስ | 11,638.8 |

ምንጭ፡ CSA,2021 እ.ኤ.አ

**ግራፍ 9: በግል ይዞታ ከተያዘ መሬት የእንሰት ምርት**





ምንጭ: CSA,2020 እ.ኤ.አ

## 4.3. ለመስኖ ልማት መዋል የሚችል የዉሃ ሀብት ያላት መሆኗ

- ➢ ኢትዮጵያ ትልልቅ የወንዝ ተፋሰሶች ያሏትና በባህላዊ እና ዘመናዊ መስኖ በመጠቀም በማልማት ላይ ትገኛለች

**ግራፍ 10: የኢትዮጵያዋና ዋናዎቹ የዉሃ ሀብቶች በመስኖ የመልማት አቅም**



*ምንጭ: የውሀ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር 2010 ዓ.ም*

## 4.4. ማዕድናት ሀብት ያላት ሀገር መሆኗ

በሀገር ውስጥ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማምጣት ማዕድናት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይም ደግሞ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን ለሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ግብአትነት እንዲውሉ በማድረግ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪን ተወዳዳሪነት መጨመርና ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

በርካታ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን እንደግብአት በመጠቀም በሀገር ውስጥ የተለያዩ ኬሚካሎችን፣ መገልገያ ቁሳቁሶችን፣ ማዳበሪያ፣ እና በርካታ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማምረት የዘርፎች ትስስርን ማጠናከር ይቻላል።

- በኢትዮጵያ ማዕድናት የሚገኙት በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በደቡብ እና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍል ሲሆን

- የብረት ማዕድናት (ወርቅ፣ ፕላቲነም፣ ብረት፣ ኒኬል፣ ክሮሚት እና ያልተለመዱ)
- የማዳበሪያ ጥሬ ዕቃዎች (ፖታሽ እና ፎስፌት)
- የከበሩ ድንጋዮች (ሰንፔር፣ ኤመራልድ፣ ኦፓል)
- የኃይል ማዕድናት (ሊቲየም፣ ግራፋይት እና ታንታለም፣ የነዳጅ ሼል እና የድንጋይ ከሰል)
- የሲሚንቶ ጥሬ ዕቃዎች (የሸክላ ድንጋይ፣ ጂፕስ፣ ጭቃ፣ ፒም)
- የሴራሚክ ጥሬ ዕቃዎች (ካኦለን፣ ፌልድስፓት) እና የመስታወት ጥሬ ዕቃ (ሲሊካ አሸዋ) እንዲሁም እብነ በረድ፣ ግራናይት ወዘተ በስፋት አሉን
- የተፈጥሮ ጋዞች እና ሃይድሮካርቦኖች እንዲሁም ሶዳ አመድ፣ ጨው ወዘተ አለን።

## 4.5 የሰዉ ሀብት

- ከሀገሪቱ ሕዝብ 57.7% በላይ የሚሆነው በአምራች ዕድሜ ክልል የሚገኝ መሆኑ በቀላሉ ሰልጥኖ ወደ ስራ ሊገባ የሚችል እና ሰልጥኖ ያለ የሰው ሀብት መኖር፤
- የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች) በመንግስትና በግል እየተስፋፉ በመምጣታቸዉ ዘርፉ የሚፈልገዉን የሰለጠነ የሰዉ ሀብት ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ መኖሩ፤

- ቅድሚያ ለተሰጣቸዉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፎች ድጋፍ የሚያደርጉ የልማት ምርምርና ጥናት ማዕከላት መኖራቸዉ፤

### 4.6. ሰፊ የገበያ ዕድል

- ሀገራችን 120 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት በመሆኑ ሰፊ የሀገር ዉስጥ ገበያ ያለ መሆኑ፤
- የአገሪቷ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በአፍሪቃ ቀንድ መገኘቷ ለሌሎች ክፍለ ዓለማት ቅርብና ምቹ መሆኗ፤
- በጎረቤት ላሉ በርካታ ወደቦች ቅርብና የተለያዩ የወደብ አማራጮች የምትጠቀም መሆኗ፤
- ሀገራችን የአፍርካ ነፃ ንግድ ስምምነት- የ55 ሀገራትን ገበያ ማለትም 1.4 ቢለየን ህዝብ ገበያ ዕድል በነፃ የሚንቀሳቀስበትን ገበያ መቀላቀሏ፤
- የአውሮፓ ህብረት EBA (everything But Arms ከጃፓን፣ ካናዳ፣ ቻይና፣ ቱርክ፣ አውስትሪሊያና ንዊዝላድ የቀረጥና ኮታ ነጻ የገበያ ዕድሎች እንዲሁም ከህንድ የተሰጠ አማራጭ የገበያ ዕድል ለምረቶቻችን የሚፈጥር መሆኑ፤
- በኢንዱስትሪ ፓርክ ከሚገኙ የውጭ አምራቾችና ዓለም አቀፍ ገዢዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ ዕድል መመቻቸቱ፤
- የአለም ዓቀፍና ሀገር አቀፍ ባዛርና ኤግዝቢሽን ድጋፍ መኖሩ፤

### 4.7. የመሠረተ ልማት አቅርቦት

- የመንገድ ዝርጋታ መስፋፋት፡- አገራችን ከጎረቤት አገሮች፣ ክልሎች ከክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚያስተሳስሩ መንገዶች የተገነቡና እየተገነቡ ያሉ በመሆናችው ግባአቶችንም ሆነ ምርቶች ለማዘዋወር ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፡፡ እስካሁን ድረስ በፌዴራል ደረጃ 18,367.7 ኪ.ሜ የአስፋልት  እና 12,073.1 የጠጠር መንገድ ዝርጋታ ተከናዉኗል (የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር መረጃ 2016 ዓ.ም )፤
- የባቡር ሐዲድ ዝርጋታ መስፋፈት፡- 750 ኪ.ሜ በኤሌክትሪክ የሚሰራው ባቡር ከጅቡቲ ወደብ አዲስ አበባ ግባአቶች/ ምርቶች የማመላለስ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፣ይህም ለወጪ እና ገቢ ምርቶች  ጊዜንና ዋጋን የሚቀንስ መሆኑ፤

- በአፍሪካ ትልቁ የአየር መንገድ መኖሩ፡- 22 የአገር ውስጥና 136 የውጭ አገር መዳረሻዎች ያሉት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሰውም ሆነ ለዕቃ ማጓጓዥ ሰፊ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ባህርና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት፡- አብዛኛውን የወጪና ገቢ ምርቶች/ ግባዓቶች የሚጓጓዝ ሲሆን ከአገልግሎቱ አሰጣጥና ከታሪፍ አኳያ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑ፤
- በተመጣጣኝ ዋጋ የኤሌክትሪክ ሐይል አቅርቦት መኖር፡- አገራችን ታዳሽ ኤሌክትሪክ ( የዉሃ፣ የንፋስ፣ የፀሐይና ጂኦተርማል) የማቅረብ ከፍተኛ አቅም ያላት መሆኑና የህዳሴ ግድብም የኤሌክትሪክ ሐይል አቅርቦት መጀመሩ፤

**ሠንጠረዥ 6፡** የኢትዮጵያ የሃይል እምቅ አቅም (potential)

| ቁጥር | የሃይል ምንጭ | መለኪያ | የሃይል እምቅ አቅም |
|---|---|---|---|
| 1 | ዉሃ ኃይል (Hydropower) | GW | 45 |
| 2 | ፀሐይ ኃይል ( kWh/m²/day | kWh/m2 | 5.2 |
| 3 | ንፋስ ኃይል (Wind) | GW m/s | 1350 |
| 4 | ጂኦተርማል (Geothermal) | GW | 7 |

**ምንጭ፡-** Ethiopia renewable energy potentials፡ https://www.aimspress.com/article/doi/

❖ የኢንፎርሜሽን እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ እየተስፋፋ የሚገኝ ሲሆን፣ የሞባይል ኔትዎርክንግ ሽፋን ከድምፅ አገልግሎት (voice service) አንጻር 98.4% የሀገርቱን ዜጎች ተደራሽ አድርጓል። በኢትዮጵያ ወደ 21 ሚሊዮን ህዝብ (167%) በመደበኛነት የኢንተርኔት ተጠቃሚ፣ 67 ሚሊዮን የሞባል ተጠቃሚ ይህም 53% የሀገርቱን ዘጎች የሚሸፍን ነዉ። 6.4 ሚሊን ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ፤ 612,000 ኢንስታግራም ተጠቃሚ፣ 6 ሚሊዮን ፌስቡክ ተጠቃሚ፤ 90,000 ቲዉተር ተጠቃሚ፣1.04 ሚሊየን መሰንጀር ተጠቃሚ፣ 870,000 ሊንኪደን ተቃሚ አሏት (Internews August, 2023 G.C)፤

- የፋይናንስ ተቋማት፡- በሀገሪቱ የግል እና የመንግስት የሆኑ 31 ባንኮችና እና 18 ኢንሹራንስ ካምፓኒዎች የሚገኙ መሆኑ እንዲሁም የዉጭ ምንዛሬ ፖሊሲ መሻሻሉ፤

## 4.8. የማኑፋክቸሪንግ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ የዉጭ ግንኙነት ፖሊሲ መኖሩ

- ጉልበት ተኮር፣ ቴክኖሎጂና ዕዉቀት ሽግግር ማድረግ የሚችሉ የዉጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ከሀገር ዉስጥ ባለሀብቶች ጋር የቅንጅት ኢንቨስትመንት (Joint-venture) ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ሽግግር እንዲፋጠን የሚያደርግ መሆኑ፤
- የተለያዩ የኮሙዩኒኬሽን መሳሪያዎችን በመጠቀም የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስተሪ ምርቶችን ለዓለም ገበያ የማስተዋወቅ ስራ የሚፈጸም መሆኑ፤
- ኤክስፖርት የሚሆኑ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች በአለም ገበያ ዉስጥ እንዲገባና ተወዳደሪ እንዲሆን በማመቻቸት የሀገሪቷ የዉጭ ምንዛሬ እንዲያድግ የሚያደርግ መሆኑ፤
- በዉጭ ሀገር ለሚኖሩ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን ወቅታዊ መረጃ በመስጠት በማኑፋክቸሪንግ ኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ የማመቻቸት ስራ የሚተገበር መሆኑ፤
- ከተለያዩ ሀገሮች ጋር ለጋራ ዕድገት የሚሆኑ የቴክኒካልና ፋይናንሽያል ድጋፍ ስምምነቶች መንግስት ትኩረት ሰጥቶ የሚያካሄድ መሆኑ፤
- በዓለም ገበያ ላይ ሀገራችን ተጠቃሚ እንዲትሆን የሚያስችሉ አለም ዓቀፍ ስምምነቶች የተደረጉና የሚደረጉ መሆኑ፡፡

## ክፍል አምስት

# 5. የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች እና ድጋፎች

## 5.1 ማበረታቻዎች

### 5.1.1 በኢንቨስትመንት ህጎች መሰረት የሚሰጡ ድጋፎች

❖ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ በደንብ ቁጥር 517/2014 መሰረት የሚሰጡ ድጋፎች፡-

➢ **ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ**

- መንግስት የማኑፋክቸሪግ ዘርፉን ለማበረታታት የተለያዩ የማበረታቻ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ወደ ስራ ያስገባ ሲሆን አዲስ ኢንቨስትመንት ለማቋቋም ኢንቨስት የሚያደርግ ባለሀብት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይሄዉም እንደተሰማሩበት ኢንዱስትሪ ዓይነትና የኢንቨስትመንት ቦታ የሚለያይ ሆኖ ከ 1 እስከ 6 ዓመት የሚቆይ የገቢ ግብር ክፍያ ነጻ ማበረታቻ ያገኛሉ (አባሪ 1፡ ማየት)፡፡

- ምርቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት ስለሚሰጥ ተጨማሪ የገቢ ግብር ማበረታቻ
    - ✓ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ያለ ኢንቨስትመት ሆኖ ቢያንስ 60% በመቶ የሚሆነው ምርቱን ወደ ውጭ የሚልክ ወይም ምርቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተፈቀደለት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ለሁለት ዓመት ከገቢ ግብረ ነፃ ይሆናል፡፡
    - ✓ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ባለሀብት ካቋቋመው የማምረቻ ፋብሪካ 80% በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን ምርት ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት በምርት ግብዓትነት የሚቀርብ ከሆነ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተፈቀደለት በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ለሁለት ዓመት ገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻ ያገኛል፡፡

- ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4,5 እና 6 ለተመለከቱ ገቢ ግብር ነፃ የመሆን ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆነው በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሳብ መዝገቡን አግባብ ላለው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

➢ **ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ**

- በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተዘረዘሩት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሰማራ አዲስ ኢንቨስትመንት ወይም ነባር ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

- የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት ከሀገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወይም ከአስመጪ የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዛ ዕቃዎቹን ለማምረት በግብዓትነት የዋሉት ጥሬ ዕቃዎች ወይም ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተመላሽ ይደረጋል፡

- በዚህ ደንብ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል ዕቀዎቹ ጠቅላላ ዋጋ 15% በመቶ የማይበልጥ መለዋወጫ ዕቃዎች እንደሁኔታው የማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ ከሆነበት ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ በዚህ አንቀጽ መሠረት የመለዋወጫ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት የሚቻለው በድምሩ ለአምስት ዓመታት ብቻ ነው፡፡

- ለኢንቨስትመንት ዓላማ የሚዉሉ ለዘርፉ ተፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት (ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች መመሪያ ቁጥር 942/2015 (አባሪ 2፡ ማየት) ፡፡

❖ **የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሰረት የሚሰጥ ድጋፍ**

በአዋጅ ቁጥር 768/2004 መሰረት ስድስት (6) ዓይነት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ዓይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

- የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት፤
- የቫዉቸር ሥርዓት፤

- የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት፤
- የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት፤
- የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት፤
- የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት፤

**ሀ/ የተመላሽ ቀረጥ ስርዓት**

የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ከውጭ ሀገር ቀረጥና ታክስ ከፍለው በሚያስገቡት ወይንም ለወጪ ንግድ በሀገር ውስጥ በሚገዙት ዕቃዎች ላይ የተከፈለውን ቀረጥና ታክስ በህግ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት ተሟልተው ሲገኙ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ቀረጥ ተመላሽ የሚሆንበት ስርዓት ነው፡፡

የድጋፉ ተጠቃሚዎች

የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

- አምራች ላኪዎች
- ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች
- ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች
- ላኪዎች ሲሆኑ እነዚህንም በዝርዝር ስናያቸው…

- አምራች ላኪ ማለት ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ማለት ነው፡፡

- ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ማለት ያመረተውን ምርት በጥሬ ዕቃ ወይም በከፊል በተፈበረከ ወይም ባለቀለት ዕቃ መልኩ ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለሌላ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ለላኪ የሚያቀርብ ሰው ማለት ነው፡፡

- በተመላሽ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለገባ ጥሬ ዕቃ የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ምርቱ ወደ ውጭ በተላከ ወይም ጥሬ ዕቃው ለአምራች ባስተላለፈ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

## ለ/ የቫዉቸር ስርዓት

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ከተሰጣቸው በኋላ በጉምሩክ ኮሚሽን የቫውቸር ደብተር የሚሰጥበት እና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርዓት ማለት ነው፡፡ የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ወደ ሀገር በሚያስገቡት ግብዓት ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ በቫውቸር ደብተሩ ላይ ተመዝግቦ ዕቃውን እንዲረከቡ ይደረጋል በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አምርተውም ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም የጥሬ ዕቃውን ባህሪይ መሰረት በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ለአንድ ተጨማሪ ዓመት ሊራዘምላቸው ይችላል፡፡

የድጋፉ ተጠቃሚዎች

- አምራች ላኪዎች.
- ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች.
- ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ናቸው፡፡

## ሐ/ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብርካ ስርዓት

- ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነጻ በማስገባት ወደ ፋብሪካ የሚጓጓዝበት ተመርቶም ለውጭ ገበያ የሚላከውን ምርት በጉምሩክ ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ስርዓትን ለመጠቀም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው እና የጉምሩክ ኮሚሽን የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ የማምረቻ ፋብሪካ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፣

  የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች፡-

- ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ እና
- ከላይ የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ናቸው

## መ/ የቦንድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ስርዓት

- ማለት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ምርት ማምረቻ የሚውሉ ከቀረጥ ነጻ ሆነው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችና በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱ ምርቶች የሚቀመጡበትና በጉምሩክ ኮሚሽን እና በፋብሪካው በጋራ ቁጥጥር የሚደረግበት መጋዘን ነው፣

የድጋፉ ተጠቃሚዎች

- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስሪዓቱ ተጠቃሚ ለሚሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የሰጣቸዉ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያወጣዉን መስፈርት የሚያሟላ መጋዘን ያላቸዉ ኢንዱስትሪዎች ይሆናሉ፡፡

**ሠ/ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ስርዓት**

"ቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን" ማለት ፈቃድ በተሰጠው አቅራቢ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ለአምራቾች እስኪሸጥ ድረስ የሚቀመጥበት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና በአቅራቢው ቁጥጥር የሚደረግበት መጋዘን ነው፡፡

**ረ/ የኢንዱስትሪ ቀጠና ስርዓት**

የኢንዱስትሪ ቀጠና ስርዓት ተጠቃሚዎች ወደ ሀገር ያስገቡትን ጥሬ ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ከጉምሩክ ጣቢያዎች ወደ ኢንዱስትሪዉ ቀጠና በማጓጓዝ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገባዉን ጥሬ ዕቃ እና በኢንዱስትሪ ቀጠና ተመርቶ ለዉጭ እና ለሀገር ዉስጥ ገበያ የሚቀርበዉን ምርት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይቆጣጠራል፡፡

የድጋፉ ተቃሚዎች

- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚያወጣዉን መስፈርት የሚያሟሉ በኢንዱስትሪ ቀጠና ዉስጥ የሚቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ይሆናሉ፡፡

❖ በኢንቨስትመንቶች ዉስጥ ለሚሰማሩ የዉጭ ሀገር ሰራተኞች የስራ ፍቃድ የሚሰጥበት እና ከዉጭ ሀገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያዉያን የሚሸጋገር እዉቀት እና ክህሎት አፈጻጸምን ለመመምራት የወጣ መመሪያ

- በኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለሚሰሩ የውጭ ሀገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጥበት እና ከውጭ ሀገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር እውቀት እና ክህሎት አፈፃፀምን ለመምራት የወጣ መመሪያ መሰረት በኤክስፖርት ተኮር የተሰማሩ ወይንም የሚሰማሩ ባለሀብቶች ያለባቸዉን የሙያ፣ የስራ አመራርና ክህሎት ችግር ለማሻሻል የዉጭ ባለሙያ ቀጥረዉ በሚያሰሩበት ጊዜ ከሚከፍሉት ክፍያ የስራ ግብር ነጻ በማድረግ ስርዓት ነዉ፡፡

## 5.2. ድጋፎች

### 5.2.1 የአዋጭነት ጥናቶች

መንግስት በአመምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ እና እስትራቴጂ እቅድ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ዕድገት ለማፋጠን እና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ትርፋማ እንዲሆኑ ለፕሮጀክታቸው አስፈላጊ የሆኑ የካፒታል፣ የጥሬ ዕቃ፣ የቴክኖሎጂ ፍላጎት፣ የሰው ሃይል እና ሌሎች ችግሮችን የሚፈታ የአዋጪነት የንግድ ስራ እቅድ ጥናቶች በማዘጋጀት ባለሀብቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

### 5.2.2. የአቅም ግንባታና የቴክኖሎጂ ድጋፎች

*ሀ/ የአቅም ግንባታ ድጋፍ*

የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ችግር የለየ እና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የንድፈ ሀሳብ እና የተግባር ሥልጠና እና የምክር አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪም ግብይት፣ የጥራት ምርታማነት ማሻሻያና ሌሎች መሰል ድጋፎችን በመለየት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፡፡

የሥራ ተነሳሽነትና ተወዳዳሪነትን ለማስፈን ጉልህ አስተዋፅኦ ያለቸውን የኢንተርፕርነርሺፕ እና የንግድ ሥራ ተወዳዳሪነት አመለካከት፣ክህሎትና ሥራ አመራር እና ካይዘን ስልጠና በጥናትና ፍላጎት ላይ በመመስረትና በማዘጋጀት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡በተጨማሪም የኢንዱስትሪዎች ምርት ጥራትና ምርታማነት እንዲያድግ በገበያ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ አዳዲስ ምርቶችን እንዲያቀርቡ እና ለውጤታማነት የሚያበቃቸው ተከታታይነትና አግባብነት ያለው የሙያ ክህሎት ስልጠና በመስጠት በተሰማሩበት የምርት መስኮች የሞያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ የሚያበቃ ድጋፍ እና የአለም አቀፍ ደረጃን (International Organization for Standardization) መሰረት ያደረገ የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ አስፈላጊ ሥልጠና፣ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ለ/ የቴክኖሎጂ ድጋፍ

የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍ የሚያስችል ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣በማላመድና በማሰራጨት በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት፣በቆዳ ኢንዱስትሪ፣ በምግብ፣ መጠጥ፣ በሥጋ፣ በወተት፣ በኬሚካል፣ ኮንስተራክሽን ግብዓቶች፣ ብረታብረት ኢንዱስትሪ እና በሌሎች ማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሃብቶች፣

ዩነቨርስቲዎች፣የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ የምርምርና ልማት ማዕከላት እና በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አማካኝነት የቴክኖሎጂ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

❖ **የማምረቻ ቦታ ድጋፍ**

**ሀ/ ኢንዱስትሪ ፓርኮች**

በሀገራችን ያለውን የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም የውጪ ገበያ ክፍተትን ለመሙላት እንዲቻል የውጪ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንቱ ላይ ተሳታፊ ለማድረግ እንዲቻል በፌደራል ደረጃ በየክልሉ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የተገነቡ ሲሆን በእነዚህም ፓርኮች ውስጥ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቀ ሼዶችን በመገንባት፣በተጨማሪም በፓርኩ ውስጥ የመሚገኘውን ቦታ ባለሀብቶች በራሳቸው እንዲያለሙ የሊዝ ውል በመስጠት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እና ለዉጭ ባለሀብቶች በሚዘጋጀው የመመልመያ መስፈርት መሰረት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

**ለ/ የማምረቻ ክላስተር ማእከላት አቅርቦት**

የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የክላስተር ማዕከላት አቅርቦት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ለመስሪያ ቦታ ግንባታ የሚያወጡትን ወጪዎችን ለመቀነስና እንዲሁም ዓለም አቀፍ ደረጃን የሚያሟሉ ክላስተር በመገንባት ለማቅረብ የሚያስችል አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በዚህ መሰረት  አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን በማልማት እና በማስተዳደር ዘርፉን ተወዳዳሪ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ከሚከናወኑ ተግባራት መሀከል በየክልሎች እና  በከተማ አስተዳደሮች ለክላስተር ግንባታ የሚሆን በትላልቅ ከተሞች 100ሄ/ር በመካከለኛ ከተሞች 50ሄ/ር በወረዳ 25 ሄ/ር መሬት በማዘጋጀት የከተሞችን ፕላን በጠበቀ መልኩ ሁሉንም መሰረተ ልማት ያሟላ እና ዘመናዊነታቸውን የተጠበቁ የማምረቻ ሼዶች እየተገነቡ በሚዘጋጀው የመለያ መስፈርት መሰረት ባለሀብቶች እየተለዩ በተመጣጣኝ ዋጋ በኪራይ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**ሐ/ ነባር ክላስተር**

በየክልሉ በመንግስት ካፒታል በጀት ተገንብተው እና መሰረተ ልማት ተሟልቶላቸው በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተሰማርተው ላሉ ኢንዱስተራያሊስቶች በአነስተኛ ኪራይ በስራ ላይ ያሉ ሼዶችና ባለአንድ ፣ባለሁለትና ባለአምስት ወለል ህንጻዎች የበለጠ ተጠናክረው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

### 5.2.3. የገበያ ትስስር

መንግስት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በሰጠው ልዩ ትኩረት እና የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻን ለማሳደግ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ለሀገር ውስጥ ተጫራቾች የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 ዓ.ም ቁጥር 16.20.5 መሰረት ከሀገር ውስጥ አቅረቢዎች ጋር በሚያደርጉት ወድድር (ሦስት በመቶ) ልዩ አስተያየት ይደረግባቸዋል፤ በጨረታ ማስከበሪያ በውል ማስከበሪያ እና ቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱ ካደራጃቸው አካላት የሚስጥ የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ይኖረዋል፤ ለጨረታ የተዘጋጀ የጨረታ ስነድ የአነስተኛ ተቋማት የተቋቋሙበትን የህጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለክፍያ በነጻ ይስጣቸዋል፡፡

በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በሚዘጋጁ ልዩ ልዩ ባዛር እና ኤግዝቢሽኖች ላይ ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በኢንዱስትሪ ፓርክ ከሚገኙ የውጭ አምራቾችና ዓለም አቀፍ ገዢዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲያደርጉ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### 5.2.4. የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት ድጋፍ

መንግስት ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰባቸው ካለው ዘርፎች መካከል ለጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ፣ አግሮ-ፕሮሰሲንግ እና ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ግብዓቶች በስፋት የሚያቀርብ የመንግስት ልማት ድርጅት እንደሚያስፈልግ በመገንዘቡ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅትን በማቋቋም ችግሮቹን ለመቅረፍ ሰፊ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓትን በማልማትና የአቅርቦት ተግባራትን በማከናወን፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት ምርትን በማምረት እና በመግዛት ማቅረብ፣ ከሀገር ዉስጥ ኢንዱስትሪዎች ፍጆታ በላይ የሆኑትን የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ወደ ዉጭ ሀገር በመላክ መሸጥ፣ ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ በማድረግ ሀገሪቱን ከውጭ ምንዛሪ ወጪ ለማዳንም ሆነ ገቢ በማስገኘት የኢንዱስትሪ ሽግግር ዕቅድ እንዲሳካ ለማገዝ ድርጅቱ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በክላስተር ውስጥ ሆነው ተመሳሳይ ምርት የሚያመርቱ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ በተመጣጣኝ ዋጋ ፣በጥራት፣በመጠን እና በሚፈለገው ጊዜ ማግኘት እንዲችሉ ይህንን አገልግሎት ለሚያቀርቡ የህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየኖች እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች የብድር ስርዓት በማመቻቸትና ከውጪ ሀገር ለሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች በተቀናጀና የውጪ ምንዛሬ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባበት አሰራር ላይ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### 5.2.5 የፋይናንስ ድጋፍ

❖ **የስራ ማስኬጃ የገንዘብ ብድር**

በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሰማርተዉ ለሚገኙ ባለሀብቶች እና አዲስ ለሚቋቋሙ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በየክልሉ በሚገኙ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት እና ሌሎች የመንግስት እና የግል ባንኮች የስራ ማስኬጃ ብድር ይሰጣሉ፡፡

❖ **የካፒታል ዕቃዎች (Capital goods) ሊዝ**

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና በክልል/ ከተማ አስተዳደር በተቋቋሙ የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አክሲዮን ማህበራት በመንግስት የኢኮኖሚ የትኩረት መስኮች ላይ የካፒታል ዕቃዎች (Capital goods) ለፕሮጀክቶቻቸው መጠቀም ለሚችሉ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪነግ ኢንዱስትሪዎች የካፒታል ዕቃዎችን ገዝቶ በኪራይ መልክ በማቅረብ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪያሊስቶች የፋይናስ ሊዝ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

- **የመሳሪያ ሊዝ ዓይነቶች**

**ሀ. የዱቤግዢ / Hire Purchase/**

በዱቤ ግዥ  አገልግሎት ከዉጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን ለሚተኩ የካፒታል ዕቃዎች (Capital goods)  / የኤክስፖርት ምርቶችን ለሚያመርቱ፣ በክላስተር ማዕከላት በመሰባሰብ በመስራት ላይ ላሉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት የሚሰጥ አገልግሎት ነዉ፡፡ እንደዚሁም የኪራይ ስምምነቱ  በተከራይና በአከራይ የሚደረገዉ ዉል ስምምነት ሲያበቃ እና አስፈላጊዉን ክፍያ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ተከራይ በዱቤ ግዥ አገልግሎት መሰረት የመሳሪያዉ ባለቤት ይሆናል፣ ከኢንዱስትሪያሊስቱ ምንም ዓይነት የመያዥ ዋስትና ሳይጠየቅ መሳሪያውን ሙሉ በሙሉ በብድር ባንኩ ያቀርባል፡፡

**ለ. የፋይናንስ ኪራይ /Financial Lease/**

ተጠቃሚዉ /ተከራይ ከሆኑ በተከራይና በአከራይ በሚደረገዉ የዉል ስምምነት መሰረት አስፈላጊዉን ክፍያ አጠቃሎ ሲያበቃ ተከራይ /ተጠቃሚዉ የካፒታል ዕቃዉን /ማሽኑን የመግዛት፣ የመመለስ፣ ባነሰ የኪራይ ተመን በማደስ የመጠቀም እና አከራይ ሽጦ ከሚያገኘዉ ትርፍ የመካፈል መብት አለዉ፡፡

❖ የልማት ባንክ የካፒታል ዕቃ በኪራይ ለመውሰድ የአመልካቹ መዋጮ ድርሻ (Equity Contribution)

- ባንኩ የካፒታል ዕቃዎችን እና ተያያዥ ወጪዎችን ፋይናንስ ያደርጋል፤ በሌላ በኩል አመልካቹ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ የሥራ ማስኬጃ ማለትም የደመወዝ፣ የጥሬ ዕቃዎች ግዢ፣ የቢሮ ኪራይ፣ የቢሮ መገልገያዎችንና የመሳሰሉ ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡
- በብሔራዊ ባንክ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ባንኩ የካፒታል ዕቃ ብድር የሚሰጠው እስከ 72,000,000 (ሰባ ሁለት ሚሊዬን ብር) ድረስ ለሚያወጡ የማምረቻ መሳሪያዎች ነው፡፡ ቅደመ መዋጮ ከጠቅላላ የመሳሪያ ዋጋ 15 - 20 % ባለሀብቱ መዋጮ ማድረግ  አይጠበቅበታል፡፡

❖ **ከክልል/ከተማ አስተዳደር ካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን**

ማህበራት በኪራይ ለመውሰድ የአመልካቹ መዋጮ ድርሻ (Equity Contribution)

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በኢኮኖሚው የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስና አቅርቦት በየክልሉ/ከተማ አስተዳደር በተቋቋሙ የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አክሲዮን ማህበራት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በዱቤ ግዥ አገልግሎት ከዉጭ አገር የሚገቡ ምርቶችን ለሚተኩ /የኤክስፖርት ምርቶችን ለሚያመርቱ፣ በክላስተር ማዕከላት በመሰባሰብ በመስራት ላይ ላሉ ኢንዱስትሪዎች ካላቸዉ ካፒታል 2.5% ለሚያወጡ መሳሪያዎች ከኢንዱስትሪያሊስቱ ምንም ዓይነት መያዥያ ዋስትና ሳይጠይቅ የማምረቻ መሳሪያዉን ዋጋ ከ15 እስከ 20 በመቶ ብቻ በመክፈል መሳሪያዉን ወስደዉ መጠቀም ይችላሉ፡፡

❖ **የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የሚያስገኛቸው ጥቅሞች**

- ከውጪ ተገዝተው የሚቀርቡ የማምረቻ መሳሪያዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ መደረጋቸው፤
- ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን በኪራይ በማግኘቱ ያለውን ካፒታል ለስራ ማስኬጃ የሚያውለው ስለሆነ ለካፒታል ቁጠባ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ፤
- የተከራዮችን የንግድ እንቅስቃሴ፣ የመክፈል አቅም ሁኔታና ፍላጎት መሰረት ያደረገ የክፍያ መጠንና የክፍያ ጊዜ ስምምነት ማደረግ የሚያስችል መሆኑ፤
- ተከራዩ የጥሬ ገንዘብ ፍሰቱ በዕቅድ እንዲመራ ማስቻሉ፤
- አገልግሎቱ ያለ ምንም የዋስትና መያዣ መሰጠቱ፤
- የብድር መክፈያ እፎይታ ጊዜ መሰጠቱ፤
- ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገት አስተዋጾ ማድረጉ፤

## ክፍል ስድስት


## 6. ባለሀብት መሳብ

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ለማስፋፊት አቅም ያላቸዉን የሀገር ዉስጥ እና የዉጭ ሀገር ባለሀብቶች ግንዛቤ በመፍጠር በዘርፉ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ እና ትርፋማ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

### 6.1 የኢንቨስትመንት ሂደት (The Investment Process)

የኢንቨስትመንት ሂድት በዋናነት የኢንቨስትመንት ሀሳብ ማመንጨትና ግብ ማስቀመጥ፣ ገበያ ማጥናት፣ ቢዝነስ ፕላንና የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ፣ ህጋዊ ሰዉነት ማግኘት፣ ፋይናንስ ማፈላለግ፣ መሬት ማግኘት፣ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን ማበረታቻ መጠቀም፣ ግንባታ ማካሄድና ማምረት፣ ከገቢ ግብር ነጻ ማበረታቻዎችን መጠየቅ እና ማስፋፋትን ያካትታል፡፡

**የኢንቨስትመንት ሂደት**



### 6.2 በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ባለሀብቶች/ድርጅቶች

- **በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች/ድርጅቶች**

እሴት በመጨመር ኤክስፖርት በማድረግ የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ በግብርና ጥሬ ዕቃ ኤክስፖርተርነት የተሰማሩ እና በሌሎች የአገልግሎት ዘርፍ ስራ ላይ የተሰማሩ የሀገር ዉስጥ ባለሀብቶች ወደ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲሰማሩ በመንግስት በኩል አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡

- **በኮንስትራክሽን ተቋራጮች ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች**

በኮንስትራክሽን ተቋራጭ የተሰማሩ ባለሀብቶች ያላቸዉን ሀብት ተጠቅመዉ በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያድረጉ ይበረታታሉ፡፡

- **የዩኒቨርሲቲ እና ቴክኒክና ሙያ ምሩቃን**

በቴክኒክና ሙያ እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች እየተመረቁ ናቸው፡፡ እነዚህም ሃይሎች እውቀትና ክህሎት ያላቸው ሲሆን የተለየ የፋይንናስ እና የማሽነሪ ብድር አቅርቦት የሚያረጋገጥ ስርዓት ከተዘረጋላቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን በቀላሉ ሊያንቀሳቅሱ ይችላሉ፡፡ በዚህም በኩል ትልቅ ትኩረት በመስጠት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን ማፋጠን ያስችላል

- **በማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች**

ባህለዊ የማዕድን ሥራዎችና የከበሩ ድንጋዮች ተደረጃተው እየሰሩ የሚገኙ ባለሃብቶች (ዕብነበረድ ማምረት፣የወረቅና የከበሩ ማዕድናት ማምረት፣ አሸዋ ማምረት እና የመሳሰሉት) ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲገቡ ይበረታታሉ፡፡

- **ሀብት ያፈሩ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በተናጥል/ በህበረት ስራ ማህበራት**

የግብርና የህብረት ሥራ ማህበራት፣ ሀብት ያፈሩ ሞዴል አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ያፈሩትን ሃብት በቀጣይ እሴት በሚጨምሩ የአግሮ ኢንዱስትሪዎች ላይ በተናጥል እና በጋራ በመሆን መዋዕለ ነዋያቸውን በማፍሰስ ከግብርና ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ሊያፋጥኑ ስለሚችሉ ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናሉ፡፡

- **በውጭ አገር ያሉ ዲያስፖራዎች**

የተለያዩ አገር ተመክሮዎች እንደሚያሳየው የዲስፖራ ኮሙዩኒቲ አባላት የአገሮች የውጭ ምንዛሬ አንድ ምንጭ ሲሆኑ ከዚያም ባለፈ ወደ ሀገር ውስጥ ይዘውት የሚመጡት እውቀትና ኢንቨስትመንት ቀላል አይደለም፡፡ በመሆኑም በውጭ ለሚገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን  የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን እምቅ አቅም በማስተዋወቅ እና ምልመላ በማድረግ በዘርፉ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## 7. የኢንቨስትመንት ማሳለጫ ስልቶች

የተፈጥሮ ፀጋ መሠረት ያደረገ ፣ የማኑፋክቸሪንግ ድጋፎች፣ማበረታቻዎችና መልካም አጋጣሚዎች የፕሮሞሽን ስራ የሚከናወኑባቸዉ ስልቶች፡-

- **የቴሌቪዥን ማስታወቂያ**
  - ✓ በዚህ የፕሮሞሽን ስልት ለዘረፉ የተቀመጡ የመንግስት ድጋፎችን ግልጽና ሳቢ በሆኑ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች እና የተለያዩ ዝግጅቶችን በመጠቀም ማስተዋወቅ ፡፡

- **የሬዲዮ ማስታወቂያ**
  - ✓ በድምፅ ብቻ በመጠቀም የሰሚው አዕምሮ ባልተገደበ ሁኔታ የራሱን ስዕል እንዲስል የሚፈቅድ በመሆኑ እና ብዛት ያላቸው ተከታይ ስለሚኖሩት ለዘርፉ የተቀመጡ ድጋፍና ማበረታቻ ማስተዋወቅ ፡፡

- **ድረገፅ** (Website)
  - ✓ ምስሎችን፣ ፎቶ ግራፎችንና ጹፎችን በመጠቀም በድረገጽ ማስተዋወቅ ፡፡

- **ማህበራዊ ሚዲያ**
  - ✓ ኢንቬስተር መር የሆነ ደንበኛን የመለየት እና የመሳብ ስራ ላይ ቁልፍ የሆነ ሚና

ይጫወታወቂያ

- **ግራፊክስ ዲዛይን እና የህትመት ማስታወቂያ**
  - ✓ የህትመት ውጤት የሆኑትን (ብሮሸር፣ በራሪ ወረቀት፣ ቢል ቦርድ እና ጋይድ ቡክ ) በመጠቀም ማስተዋወቅ ፡፡

- **ዘጋቢ/ዶክመንተሪ ፊልም**

- ✓ በዘርፉ የተሰሩ ዘጋቢ ፊልሞች በቴሌቪዥን ቻናሎችና ማህበራዊ ድህረ-ገጾች ማስተዋወቅ፡

- **የሁነት ስልቶች ( Event)**
  - ✓ የተለያዩ አዝናኝ፣ ቀስቃሽ፣ አበረታች፣ አስተማሪ ሁነቶች በማዘጋጀት መልዕክት ማስተላለፍ ያስፈልጋል፡፡

- **ስፖንሰር ማድረግ**
  - ✓ የተለያዩ በመደበኛነት እና በቀጥታ ስርጭት የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን ስፖንሰር በማድረግ ዘርፉን ማስተዋወቅ፡፡

- **የህዝብ ብግንኙነት ስልት**
  - ✓ ለዜና የሚሆኑ የዘርፉን መረጃዎች በማዘጋጀት ወደ ቴሌቭዥብ ጣቢያ፣ ሬዲዮ ጋዜጦችና ሚዲያዎች እንዲደርሳቸው በማድረግ ማስተዋወቅ ፡፡
  - ✓ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች በማጥናትና በመመልመል በቀጥታ በመነጋገርና በማሳመን መሳብ

- **አቻ ለአቻ (peer-to-peer) ስልት**

## ክፍል ስምንት

## 8. የንግድ ድርጅት ምስረታ አይነቶች

### 8.1 የንግድ ድርጅት አይነቶች

- በሀገራችን ሶስት አይነት የንግድ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን እነሱም፡- የግለሰብ ነጋዴ፣የንግድ ማህበራት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው፡፡

እነዚህ የንግድ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው የተለያየ ባህሪና ውስጣዊ አደረጃጀት ያላቸው ሲሆን የተለያየ ጠቀሜታም አላቸው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ወደ ንግድ ተግባር ከመግባቱ በፊት ከእነዚህ የንግድ ድርጅት አይነቶች የበለጠ የሚስማማቸውን በመምረጥ ህጋዊ እውቀና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የተሻለ የሚሉትን ለመምረጥ ደግሞ ስለእያንዳንድ የንግድ ድርጅት አይነት በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች በብዛት የተቋቋሙበት የንግድ ድርጅቶች እንደሚከተለዉ ተቀምጧል፡፡

### 1. የግል ኢንተርኘራይዝ

ይህ የንግድ ድርጅት አይነት በአንድ ሰው የግል ሀብት የሚመሰረትና የሚተዳደር ሲሆን የድርጅቱ ባለቤት በድርጅቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ብቸኛ ውሳኔ ሰጭ የሆነበት ነው፡፡ የዚህ አይነት ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ ብዙ ካፒታልና ሙያዊ የሆነ እውቀት የማይጠይቁ ሥራዎች ላይ ሰዎች በቀላሉ የንግድ ፈቃድ አውጥተው የራሳቸውን የንግድ ሥራ የሚመሰርቱበት አደረጃጀት ነው፡፡ በመሆኑም ብዙ ሰዎች የሚመርጡትና የተጠቃሚዎች ቁጥር ከሌሎች የአደረጃጀት አይነቶች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ ነው፡፡

#### ሀ/ የግል ኢንተርፕራይዝ ጠቀሜታው

በአንድ ግለሰብ የሚመሰረቱ የንግድ ድርጅቶች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

- **በቀላሉ የሚመሰረት መሆኑ**፡- የዚህ አይነት የንግድ ድርጅት ለመመስረት ከሌሎች ሰዎች ጋር መሻረክ፣ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ወዘተ. የማይጠይቅና ሙሉ በሙሉ በግለሰቡ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሂደቱን ቀላል የያደርገዋል፡፡ አንድ ግለሰብ በፈለገው ሙያ፣ በፈለገው ጊዜና ቦታ ንግዱን የመመስረት ሙሉ ነፃነት አለው፡፡

- **በአነስተኛ ካፒታል ይመሰረታል፡-** የዚህ አይነት የንግድ ድርጅት ለመመስረት የሚያስፈልገውን የካፒታል መጠን የሚወስን ህግ ባይኖርም ግለሰቡ የመረጠውን የንግድ ሥራ ማስኬድ አስከቻለ ድረት አነስተኛ በሆነ ካፒታል ሊመሰረት ይችላል፡፡
- **የንግድ ሥራው ብቸኛ ተጠቃሚ መሆኑ፡-** የንግድ ሥራው የሚመራውና የሚተዳደረው በአንድ ግለሰብ እንደመሆኑ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ጥቅምም እንዲሁ ብቸኛ ተጠቃሚ ይሄው ግለሰብ ይሆናል ማለት ነው፡፡

## 2. የንግድ ማህበራት

የንግድ ማህበራት ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ዕውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን አዋጥተው በጋራ ለመስራት ተስማምተው የሚመሰርቱት የንግድ ድርጅት አይነት ነው፡፡ ካሉት የንግድ ማህበራት አደረጃጀቶች ዉስጥ የአነስተኛና መከካለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች በብዛት ተደራጅተዉ እየሰሩበት ያሉት፡-

ሀ. ተራ የሽርክና ማህበር /Ordinary Partnership/

ለ. የህብረት ሽርክና ማህበር /General Partnership/

ሐ. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /Private Limited Company/ ናቸው፡፡

እነዚህን የንግድ ማህበራት በአንድ ግለሰብ ከሚመሰረቱ የንግድ ድርጅቶች የሚለዩት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቁና ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የሚተዳደር መሆኑ ሲሆን ትላልቅና ዘርፈ ብዙ ተግባራት ያላቸውን የንግድ ድርጅቶች ለመመስረት ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

### ሀ. ተራ የሽርክና ማህበር /Ordinary Partnership/

ተራ የሽርክና ማህበር የሚባለው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በጥሬ ገንዘብ፣ በአይነት ወይም በሌላ መንገድ መዋጮ አድርገው በጋራ የሚመሰርቱት የንግድ ድርጅት ነው፡፡

### ለ. የህብረት ሽርክና ማህበር /General Partnership/

የህብረት ሽርክና ማህበር የማህበርተኞች እያንዳንዳቸው በአንድነትና ሳይከፋፈል እርስ በርሳቸውና ለማህበሩ ግዴታዎች ሀላፊዎች የሚሆኑበት ማህበር ነው፡፡ ይህም ማለት ማህበሩ ለሚያጋጥመው

አደጋ ወይም እዳ ሁሉ እያንዳንዱ አባል በግሉ፣ ወይም ሁሉም በአንድነት ወይም ከሁሉም የተወሰኑት ብቻ በተናጥል ለእዳው ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

የህብረት ሽርክና ማህበር የተቋቋመው ለንግድ ዓላማ ከሆነም ማህበርተኞቹ እንደነጋዴ ይቆጠራሉ፡፡ ይህ አይነቱ ማህበር ሲመሰረት በንግድ መዝገብ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ማህበሩ መብት የማግኘትና የግዴታ ውል የመግባት እና እንዲሁም በማህበሩ ስም በፍርድ ቤቶች መክሰስ ወይም መከሰስ ይችላል፡፡

## የሽርክና ማህበር ጠቀሜታው

- **በቀላሉ ለመመስረት የሚቻል መሆኑ፡-** ከሌሎች ማህበራት ጋር ሲነፃፀር የሽርክና ማህበርን ለመመስረት የሚወስደው ጊዜና ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ በቀላሉ ህጋዊነትን በማግኘት ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት ያስችላል፡፡
- **በአነስተኛ ካፒታል መመስረት የሚቻል መሆኑ፡-** ከግለሰብ ነጋዴ ቀጥሎ በአነስተኛ ካፒታል ልንመሰርተው የምንችለው የንግድ ማህበር የሽርክና ማህበር ነው፡፡
- **የተሻለ ካፒታል ለማሰባሰብ የሚያስችል መሆኑ፡-** የሽርክና ማህበራት ከግለሰብ ነጋዴ የሚለዩት ሁለትና ከሁለት በላይ ሆነው የሚመሰርቱት በመሆኑ እያንዳንዳቸው ሽሪኮች ከግለሰብ ነጋዴ የተሻለ በዓይነትና በገንዘብ በማዋጣት ካፒታላቸውን የተሻለ ማድረግ መቻላቸው ነው፡፡ የተሻለ ካፒታል ማዋጣት ከቻሉ ደግሞ የተሻለ የንግድ ሥራ ላይ የተሻለ አቅም ኢንቨስት ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

### ሐ/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /Private Limited Company/

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ማለት ማናቸውም ማህበርተኛ ካስገባው መዋጮ በላይ ኃላፊ የማይሆንበት ማህበር ማለት ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ማህበር የአባላት ቁጥር አንድ እና ከሃምሳ ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

### ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጥቅም

- *ኃላፊነተ የተወሰነ መሆኑ፡-* እንደ አክሲዮን ማህበራት ሁሉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮኖች በማህበሩ ላይ ካላቸው ድርሻ በላይ በእዳ ሊጠየቁ አይችሉም፡፡

- ያልተገደበ የጊዜ ቆይታ ያላቸው መሆኑ፡- ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በተወሰኑ አባላት የግል ሁኔታ ህልውና በቀላሉ አደጋ ላይ ሊወድቅ አይችልም፡፡ ስለዚህ በገበያው ውስጥ ረጅም ጊዜ የመቆየት እድል አለው፡፡
- ካፒታሉን ለማሳደግ ቀላል መሆኑ፡- ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ በመሆኑና ከፋይናንስ ተቋማት በቀላሉ ብድር ማግኘት የሚችል በመሆኑ ካፒታሉን ለማሳደግና ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል፡፡

### 3/ የኅብረት ሥራ ማህበራት /Cooperative Societies/

የኅብረት ሥራ ማህበር ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ነው፡፡ የማህበር አባለት ቁጥር ዝቅተኛው አስር ነዉ፡፡

## ማጣቀሻ (Reference)


- የኢ.ፌዲ.ሪ. አምራች ኢንዱስትሪ ፖሊስ 2016 ዓ.ም
- ደንብ ቁጥር 526/2015 የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ፣
- ኢንዱስትሪ ሚኒስተር ብሔራዊ የአምራች ዘርፍ ተኪ ምርት ስትራቴጂ 2016 ዓ.ም
- Ethiopia Manufacturing SME Development Roadmap, 2023 G.C.
- Investment Potentials In Ethiopia Ethiopa Envestment Commission,2022 G.C.
- የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዕቅድ 2012 — 2022 E.C.
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት፤
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊስ ታህሳስ 2016 ዓ..ም፤
- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ደንብ ቁጥር 517/2014 ፤
- የገንዘብ ሚኒስቴር ለልማት ፕሮጀክቶች እንዲዉሉ ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች መመሪያ ቁጥር 942/2015፤
- የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004፤
- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለሚሰሩ የውጭ አገር ሰራተኞች የስራ ፈቃድ የሚሰጥበት እና ከውጭ አገር ሰራተኞች ወደ ኢትዮጵያውያን የሚሸጋገር እውቀት እና ክህሎት አፈፃፀምን ለመምራት የወጣ መመሪያ 2013 ዓ.ም፤
- የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድኅረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 935/2015
- UNDP working paper series No. 4, Ethiopia, 2023 G.C
- https://www.britannica.com/event/Industrial-Revolution
- United Nations Economic and Social Commission for Asia and the Pacific (UNESCAP), Published periodically various years.
- UNDP,2023 Can Ethiopia Become a Manufacturing Powerhouse? N0.4 Working Paper Series.
- Ethiopia renewable energy potentials፡ https://www.aimspress.com/article/doi/

**አባሪ 1፦ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር 517/2014 የገቢ ግብር ማበረታቻ**

| የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|
| 1.1. የምግብ ኢንዱስትሪ | | |
| 1.1.1. ሥጋና የሥጋ ውጤቶች ማቀነባበርና መጠበቅ | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.2. ዓሣና የዓሳ ውጤቶችን ማቀነባበር | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.3. አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባርና መጠበቅ | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.4. የምግብ ዘይት ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.5. ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶች ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.6. የምግብ ማሻሻያ፣ ተጨማሪዎች ወይም ንጥረ ነገሮች ወይም ስታርችና የስታርች ውጤቶችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.7. የእህል ምርት ውጤቶችን ማቀነባበር (ዱቄት ማምረትን ሳይጨምር) | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.8. ስኳር ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.9. መኮሮኒ፣ፓስታ እና/ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.10. አዮዲን የተጨመረበት ጨው ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.11. ሰው ሰራሽ ማር ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.12. ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.1.13. የእንስሳት መኖ ማቀነባበር | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|
| 1.2. የመጠጥ ኢንዱስትሪ | | |
| 1.2.1. የአልኮል መጠጥ ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.2.2. የወይን ጠጅ ማምረቻ | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.2.3. ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.2.4. የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎች ውሃዎችን ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.2.5. ለስላሳ መጠጥ ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.3. የጨርቃ ጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.3.1. የተለያዩ የጨርቃጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀት፣ መፍተል፣ መሸመን፣ ማጠናቀቅ እና/ወይም ማተም (አልባሳትን ሳይጨምር) | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.3.2. ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተሸ በማፍካት፣ በማጠንር ወርድንና ቁመቱን እንደጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.3.3. ከአልባት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆች ወይም ሹራብ ወይም ፎጣ ወይም ምንጣፍ ማምረት | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.3.4. የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳት ጨምሮ) | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | |
|---|---|---|
| ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | | |
| 1.4. የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.4.1. ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ (ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋትን አይጨምርም) | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.4.2. ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
| 1.4.3. የቆዳ ውጤቶች እና/ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.4.4. የቆዳ ወይም የቆዳ ምትክ ጫማ ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.5. የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.5.1. የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅን፣ ጣውላ ማምረትን እና ቀድመው የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶችን መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.6. የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.6.1. ፐልፕ እና/ወይም ወረቀት ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.6.2. የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.7. የማተሚያ ኢንዱስትሪ | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 1.8. የኬሚካና የኬሚካ ውቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.8.1. መሠረታዊ ኬሚካችን | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ |

| | | |
|---|---|---|
| (ኢታኖልን እ/ወይ ሰው ሰራሽ ጭረቶች ጨምሮ)፤ እና/ወይም ሃይድሮጂን እ አሞቒያ ማምረት | የመሆን | የመሆን |
| 1.8.2. ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶች ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.8.3. መሠረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) ፕላስቲኮችን እነ/ወይ ሲንቴቲክ (ሰው ሰራሽ) ጎማ ጥሬ ዕቃዎችንና ጎማ ውጤቶችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.8.4. ጸረ-ተባይና የግብርና ኬሚካሎችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.8.5. ቀለም ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች፣ ማጣበቂያ እና/ወይም መሠረታዊ ያልሆኑ ኬሚካሎችን ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.8.6. የንፅህናና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች እና ግብዓቶች መፈብረክ | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.9. የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ | | |
| 1.9.1. ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.9.2. ለሰው አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.9.3. ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.9.4. ከመድኃኒት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የማሸጊያ ምርቶች ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.9.5. የመድኃኒት ማሸግ ሥራዎች | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.10. የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |

| | | |
|---|---|---|
| 1.10.1. ፌስታልን ሳይጨመር የፕስቲክ ውጤቶችን ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.11. ብረት ያሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.11.1. መስታወት እና/ወይም የመስታወት ወይም የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.11.2. ሲሚንቶ ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.11.3. የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶች ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም |
| 1.11.4. የካባ ድንጋዮችን ማውጣት ሳይጨምር የድንጋይ ውጤቶችን፣ ዕብነ በረድ እና ግራናይት የኖ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርጽ ማውጣት እና ማጠናቀቅ | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.11.5. ኖራ፣ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉት መለሰኛዎችን ማምረት | የገቢ ግብር ማበረታቻ አያገኝም | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| የኢንቨስትመንት መስክ | በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | በሌሎች አካባቢዎች |
|---|---|---|
| 1.12. የመሰረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ /የማዕድን ማውጣትን ሳይጨምር/ | | |
| 1.12.1. ብረት፣ የአረብ ብረት እና የብረት ማዕድናት ውውቶችን መፈብረክ | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.12.2. መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.12.3. ከብረት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ/ማድለብና የተለያዩ ቅርፆችን ማውጣት | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.13. የስትራክቸር የሚያገለግሉ የብረታ ብረት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.13.1. የማዋቀሪያ እና የተለያዩ የብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት (የቤታ ክዳን ቆርቆሮንና ሚስማር ሳይጨምር) | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.14. የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.14.1. ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን እና/ወይም የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.14.2. የመገናኛ መሣሪያዎች ወይም የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስስቴሌቪዥን፣ ዲቪዲ፣ ሬዲዮ እና የመሳሰሉት/ዕቃዎችን ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.14.3. የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.14.4. የህክምና መሳሪያዎችን | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ | ለ5 ዓመት ከገቢ |

| | | |
|---|---|---|
| ወይም አቅርቦቶችን ማምረት | የመሆን | ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.14.5. የህክምና መሳሪያዎችን መገጣጠም | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.14.6. የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ወይም መገነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያ ዕቃዎችን ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.15. የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ | | |
| የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.16. የማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ | | |
| 1.16.1. ለሁለገብ አገልግሎት ስራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6ብር ነፃ የመሆን |
| 1.16.2. ለልዩ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6ብር ነፃ የመሆን |
| 1.17. የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሣሪያዎች ማምረት | | |
| 1.17.1. የሞተር ተሽከርካሪን(መኪና) ማምረት | ለ3ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ4 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.17.2. የመኪነ አካት፣ ተሳታችን እና/ወይም ከፊል ተሳታችን ወይም መለዋወጫዎች እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.17.3. በባቡር እና በትራም መንገድ የሚሄዱ ሎኮሞቲቮችን እንዲሁም ዘዋሪ እግር ያላቸውን ተሽከርካሪዎችን እና ጋጋሪዎችን ማምረት | ለ5ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ6 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.17.4. የሞተር ብስክቶችን፣ ብስክሌቶችን እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.17.5. ጀልባዎችን መገንባት | ለ2ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ3 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

| | | |
|---|---|---|
| 1.18. የቤትና ዱሮ ዕቃዎች (ከሴራክ የሚሰሩትን ሳይጨምር) ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.19. የእደጥበብ፣ የገፀበረከት ዕቃዎችች አርቴፊሻል ጌጣጌጥ፣ የሙዚቃ እና የስፖርት ዕቃዎችን ማምረት | ለ1ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ2 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.20. ከግብርና ጋር የተቀናጀ የማምረት ኢንዱስትሪ | ለ4ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.21. የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርክን ጨምሮ፣ ማልማት እና የማከራየት ሥራዎች | ለ 10 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ15 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |

አባሪ 2፡ ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ

ተሽከርካሪዎች መመሪያ ቁጥር 942/2015

| የኢንቨስትመንት ስራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 1.የምግብ ኢንዱስትሪ | | | | |
| 1.1 ሥጋና የሥጋ ውጤቶች ማቀነባበር | ሁለት | አንድ | ሰስት | ሁለት |
| 1.2 ዓሣና የዓሣ ውጤቶች ማቀነባበር | ሁለት | አንድ | ሶስት | ሁለት |
| 1.3 አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበርና መጠበቅ | ሁለት | አንድ | ሶስት | ሁለት |
| 1.4 የምግብ ዘይት ማምረት | አንድ | በሚያስፈልገው መጠን | አንድ | በሚያስፈልገው መጠን |
| 1.5 ወተት ማቀነባበርና /ወይም የወተት ውጤቶችማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.6 የምግብ ማሻሻያ፣ተጨማሪዎች ወይም ንጥረ ነገሮች ወይም ስታርችና የስታርች ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.7 የእህል ምርት ውጤቶችን ማቀነባበር( የዱቄት ማምረትን ሳይጨምር) | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 1.8 ስኳር ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.9 ማካሮኒ ፓስታ እና / ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.10 አይዮዲን የተመረበት ጨው ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 1.11 ሰው ሰራሽ ማር ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 1.12 ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 1.13 የእንስሳት መኖ ማቀነባበር | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 2.የመጠጥ ኢንዱስትሪ | | | | |
| 2.1 የአልኮል መጠጥ ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.2 የወይን ጠጅ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.3 ቢራ እና /ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.4 የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎች ውሃዎችን ማምረት | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሶስት |
| 2.5 ለስላሳ መጠጥ ማምረት | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሶስት |
| 3.የጨርቃጨርቀረና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3.1 የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀት፣ መፍተል፣ መሸመን፣ ማጠናቀቅነቀ እና/ ወይም ማተም (አልባሳትን ሳይጨምር) | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.2 ጣቃ ጨርቅ፣ ክር ፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትን ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት ማቅለም፣ በማኮማተር ፣ በማፍካት፣ በማጠንከር፣ወርድን ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.3 ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆችን ወይም ሹራብ ፎጣ ወይም ምንጣፍ ማምረት | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.4 የጨርቃጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልበሳትን ጨምሮ) ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 4.የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 4.1 ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ (ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋትን አይጨምርም) | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 4.2 ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 4.3 የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ወይም ተጓዳኝ አካላትን (አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 4.4 ቆዳ ወይም የቆዳ ምትክ ጫማ ማምረት | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 5.የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 5.1 .የእንጨት ውጤቶች (እንጨት መሰንጠቅ ፣ ጣውላ ማምረት እና ቀድመው የተዘጋጁ .የእንጨት ውጤቶች መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 6.የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 6.1 ፐልፕ እና /ወይም ወረቀት ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 6.2 የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 7.የማተሚያ ኢንዱስትሪ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 8.የኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 8.1 መሰረታዊ ኬሚካሎችን ( ኢታኖልን እና / ወይም ሰው ሰራሽ ጭረቶችን ጨምሮ ) እና/ ወይም ሀይዲሮጂን እና አሞኒያ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 8.2 ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሪጂን ውህዶችን ማምረት | አይፈቀድም | በሚያስፈልገው መጠን | አይፈቀድም | በሚያስፈልገው መጠን |
| 8.3 መሰረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ ) የፕላስቲክ እና/ ወይም ሲንቴቲክ(ሰው ሰራሽ) ጎማ ጥሬ ዕቃዎችን እና ጎማ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 8.4 ፀረ-ተባይ የግብርና ኬሚካሎችን ማምረት | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 8.5 ቀለም፣ ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች፣ ማጣበቂያ እና /ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ኬሚካሎችን ማምረት | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 8.6 የንጽህናና የኮስሞቲክስ እቃዎችንና ግብአቶችንማምረት | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 9.መሰረታ መድኃኒት ምርት የመድኃኒት ኢንዱስትሪ | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9.1 ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሰረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 9.2 ለሰው አገልግሎት የሚውሉ መድኃኒቶችን ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 9.3 ለእንስሳት የሚውሉ መድኃኒቶችን ማምረት (ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 9.4 ከመድኃኒት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የማሸጊያ ምርቶችን ማምረት | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 9.5 የመድኃኒት ማሸግ ስራዎች | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| <u>10.የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 10.1 ፌስታልን ሳይጨምር የፕላስቲክ ውጠየቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አይፈቀ ድም | አይፈቀድም | አይፈቀ ድም |
| <u>11.ብትን ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 11.1 መስታወት እና/ወይም የመስታዎት ወይም የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 11.2 ሲሚንቶ ማምረት | አይፈቀድም | በሚያስፈል ገው መጠን | አይፈቀድም | በሚያስፈ ልገው መጠን |
| 11.3 የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.4 የካባ ድንጋዮችን ማውጣት ሳይጨምር ጠድንጋይ ውጤቶችን፣ እምነበረድና ግራናይት የኖራ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርጽ ማውጣት እና ማጠናቀቅ | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.5 ኖራ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን መምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| <u>12.የመሰረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ (ማዕድን ማውጣትን ሳይጨምር)</u> | | | አይፈቀድም | |
| 12.1 ብረት፣ የአረብ ብረት እና የብረት ማዕድናት ውጤቶችን መፈብረክ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 12.2 መሰረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 12.3 ከብረትና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ /ማድለብና የተለያዩ ቅርጾችን ማውጣት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| <u>13. ለስትራክቸር የሚያገለግሉ የብረታ ብርት</u> ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 13.1 የማዋቀሪያና የተለያዩ ብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት ( የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና ሚስማርን ሳይጨምር) | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| <u>14.የኮምፒውተር ኤሌክሮኒክስ እና የእይታ እቃዎች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 14.1 ኮምፒውተር እና ተጓኝ እቃዎችን እና /ወይም የኤሌክሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.2 የመገናኛ መሳሪያዎችን ወይም የፍጆታ ኤሌክሮኒክስ (ቴሌቭዥን፣ዲቪዲ፣ሬዲዮና የመሳሰሉትን) ዕቃዎች ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.3 የመለኪያ ‹ የመተንፈሻ፣ የመቃኛ፣የመቆጣጠሪያ | አንድ | አይፈቀ | አንድ | አይፈቀ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መሳሪያዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | | ድም | | ድም |
| 14.4 የህክምና መሳሪያዎችን ወይም አቅርቦቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.5 የህክምና መሳሪያዎችን መገጣጠም | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.6 የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ወይም መግነጢሳዊ እና የእይታ ሚዲያ እቃዎቸን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| <u>15.የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 15.1 .የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| <u>16.የማምረቻ /አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎችና ዕቃዎች አንዱስትሪ</u> | | | | |
| 16.1 ለሁለገብ አገለወግሎት ስራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 16.2 ለልዩ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| <u>17.የመጓጓዣ ተሽከርካሮዎችና ሌሎች የትራንስፖርት መሳሪያዎችን ማምረት</u> | | | | |
| 17.1 የሞተር ተሽከርካሪ (መኪና) ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.2 የመኪና አካላትን፣ ተጎታች እና /ወይም ከፊል ተጎታችን ወይም መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.3 በባቡርና በትራም መንገድ የሚሄዱ ሎኮሞቲቮችን እንዲሁም ዘዋሪ እግር ያላቸውን ተሽከርካሪ ጋሪዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.4 የሞተር ብስክሌቶችን ብስክሌቶችን እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.5 ጀልባዎችን መገንባት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 18. የቤትና የቢሮ ዕቃዎች (ከሴራሚክስ የሚሰሩትን ሳይጨምር) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 19. የዕደጥበብ ፣ የገፀበረከት ዕቃዎች፣ አርቲፊሻል ጌጣጌጥ፣ የሙዚቃ ዕቃዎች እና የስፖርት ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 20.ከግብርና ጋር የተቀኛጀ የማምረት ኢንዱስትሪ | ሁለት | ሦስት | ሦስት | አራት |
| 21.የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ጼክኖሎጂ ፓርክን ጨምሮ ማልማትና ማከራየት ስራዎች | ሁለት | ሦስት | ሦስት | አራት |

## አባሪ 3. ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተኪ ምርቶች ዝርዝር

### i. የምግብ እና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ አጭር (1 — 3) | መካከለኛ (4 — 7) | ረጅም (8 — 10) |
|---|---|---|---|---|---|
| ምግብ እና መጠጥ | ሰብል | ብቅል | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ሰብል | ፓስታ እና ማካሮኒ | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ስኳር | ስኳር፣ ጣፋጭ ምግቦች | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | የቅባት ዕህሎች | የምግብ ዘይት | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | አትክልና ፍራፍሬ | የፍራፍሬ ጭማቂ፣ የማንጎ ፐልፐ፣ የማንጎ ኮንሰንትሬት | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | የምግብ ዝግጅት | የምግብ ዝግጅት* | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ሰብል | የበቆሎ ዱቄት፣ በቆሎ ፍሌክስ፣ በቆሎ ስታርች እና በቆሎ ስናክ | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ሰብል | የዳቦ መጋገሪያ ምርቶች፣ ብስኩት፣ ኬክስ | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ሰብል | የስንዴ ወይም የሜስሊን ዱቄት | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ተረፈ ምርት | የእንስሳት መኖ | | | |
| ምግብ እና መጠጥ | ተረፈ ምርት | የበለጸጉ ምግቦች (CSB+፣ CSB++፣ famix) | | | |

## ii. የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር (1 — | መካከለኛ | ረጅም (8 — |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሾረበ) | ሱሪ፣ ቱታ፣ ቁምጣ | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሾረበ) | የወንዶች ወይም የወንድ ልጅ የውስጥ ሱሪ (አጫጭር፣ ቦክሰር፣ ሱሪዎች፣ ወዘተ) | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሾረበ) | እንደ ጃምፐሱት፣ ሮምፐርስ፣ ታንክ ቶፕ እና ሙሉ ልብሶች (ባለ3 ፣ ባለ5 ፣ ባለ 7 ፣ ወዘተ ብዛት ያለው) ከጥጥ እና | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሾረበ) | ከጥጥ የተሰሩ ቲሸርቶች፣ ነጠላ ጫማዎች፣ ታንክ ቶፖች እና ሌሎች እጅጌ የሌላቸው የላይኛው | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሾረበ) | ረጅም ወይም አጭር ስቶኪንጎች፣ ካልሲዎች እና ተመሳሳይ የስቶኪንጎችን አይነቶች | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመኑ ጨርቆች የተሰሩ የምሽት ልብሶች እና ፒጃማዎች | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሱፍ ያልተሰራ የሱፍ አይነት ኮትና እና ጃኬት | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሠሩ የወንዶች ወይም የወንድ ሸሚዞች | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ አንገት ወይም ትከሻ ላይ የሚለበሱ ስካርቮች እና ተመሳሳይ ነገሮች | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ካልተሸመኑ የተሠሩ ልብሶች | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር (1 — | | | መካከለኛ | | | | ረጅም (8 — | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ሰው ሰራሽ ብትን ጭረቶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ካርድ ያልተደረጉ ፣ ክር ያልሆኑ ወይም በሌላ መንገድ ያልተሰሩ አጫጭር የፖሌስተር | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | የጥጥ ተረፈ ምርቶች (የክርና የተሰበሰበ የአልባሳት) ተረፈ ምርቶችን ሳይጨምር | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ሰው ሰራሽ የአሲቴት ብትን ጭረቶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ያለተበጠረና ያልተሳገ ጥጥ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ሸካራማ የፖሊስተር ክር | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከረጃጅም ፖሊስተር ጭረቶች የተሰራ ክር | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከአይሪሊክ ወይም ከሞዳክሪሊክ ጭረቶች ተሰርቶ የተቀለመና በኬብል መልክ የተሰራ ክር | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከፖሊስተር ጭረቶች የተሰራ በኬብል መልክ የተሰራ/የተገመደ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከረጃጅም የፖሌስተር ጭረቶች የተሰራ ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከሰው ሠራሽ ጭረቶች የተሰራ የሰፌት ክር | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ሽምን ጨርቅ) | ≥ 85% ቴክስቸርድ እና ቴክስቸርድ ያልሆነ ፖሊስተር ጭረቶች የተሰሩ ጨርቆች | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር (1 — | | | መካከለኛ | | | | ረጅም (8 — | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ሽምን ጨርቅ) | ከተለያዩ ከፍተኛ ጥንካሬ ካላቸው ሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ሽምን ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ሽምን ጨርቅ) | ከ85% በሚበልጡ ቴክስቸራይዝድ ፖሊስተር የተሰሩ የተቀለሙ የተሰሩ ሽምን ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከጥጥና ከሰው ሰራሽ ጭረቶች ውጭ የተሰሩ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከተለጣጭ ጭረቶች የተሰሩ የተሸረቡ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | የተሸረቡ ረጅም ፀጉራም ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ተለጣጭ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም እትም | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ተለጣጭ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም የተቀለሙ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም ረጃጅም ሉፖች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ያልተሸመነ ጨርቅ) | ከ25-150 ግ/ሜ² የሚገዝፉ ከሳውሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ያልተሸመኑ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በተፍቲንግ፣ በመርፌ፣ በመንጠቆ፣ ወዘተ የቴክኒኮች አይነቶች የተሰሩ ምንጣፎች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በፒቪሲ የተሸፈነ/የተለበጠ ጨርቅ | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ (በአመታት) | | | | | | | | | |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | አጭር (1 — 3) | | | መካከለኛ (4 — 7) | | | | ረጅም (8 — 10) | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | የጎማ ገመድ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከእንስሳት ፀጉር ክሮች የተሠሩ ምንጣፎች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከ30 ሴ.ሜ ወርድ ያልለጡ ከተለጣጭ/የጎማ ክር ና ያለ ወይም | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በፕላስቲክ የተለበጡ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከ30 ሴ.ሜ ወርድ ያልበለጡ እና በጥጥ ወይም ሰው ሰራሽ ጭረቶች ያልተሰሩ ጠባብ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከዕፅዋት ጭረቶች ወይም ከወፍራም የእንስሳት ፀጉር የተሠሩ ምንጣፎች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከጥጥ የተሰራ እና ለህክምና አገልግሎት የሚውል ቀላል ክብደት ያለው ጨርቅ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በቁጥርጥር የተሰሩ የምንጣፍ ጨርቅ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ቴክኒካል ቴክስታይል (ከሚለበስ ውጭ ለሆነ አገልግሎት) | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ክሮች፣ ጭረቶች፣ ወዘተ በመሃል ሽመና የተሰራ የተጠለፈ ጨርቅ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸረበ) | ከጥጥ ውጭ የተሰሩ ቲሸርቶች፣ ጃፖኒዎች፣ ታንክ ቶፖች እና ሌሎች ሌሎች እጅጌ አልባ ልብሶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸረበ) | የሱፍ እና የእንስሳት ፀጉር ውጭ የሆኑ የስፖርት ቲሸርቶች፣ እጅጌ የሌላቸው ቲሸርቶች፣ ኮሌታ ያላቸው ወይም ኮሌታ የሌላቸው | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ (በአመታት) | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር (1 — 3) | | | መካከለኛ (4 — 7) | | | | ረጅም (8 — 10) | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸረበ) | በሱፍ እና የእንስሳት ፀጉር የተሰሩ የስፖርት ቲሸርቶች፣ እጅጌ የሌላቸው ቲሸርቶች፣ ኮፊያ ያላቸው ወይም ኮፊያ የሌላቸው ሹራቦች፣ ካርዲጋኖች (ሹራብ ጃኬቶች) | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸረበ) | ከጥጥ እና ሰው ከሠራሽ ጭረቶች ያልተሰሩ እንደ ጃምፐሱት፣ ሮምፐርስ፣ ታንክ ቶፕ፣ ሙሉ ልብሶች (ባለ 3፣በለ 5 እና በለ 7 ብዛት ወዘተ) ያሉ የተለያዩ የጨቅላ ወይም የጨቅላ አልባሳት | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸረበ) | የስፖርት ሱሪ እና ጃኬት በሴት | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸረበ) | ጃኬት የሚመስሉ ልብሶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ሱሪ፣ ቁምጣ፣ ቱታ ወይም አጠቃላይ ከተሸመነ ጨርቅ የተሰራ ልብስ | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ የስፖርት ሱሪዎች እና ጃኬቶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ አልባሳት | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመነ ጨርቅ የተሠሩ ጃኬት የሚመስሉ ልብሶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሱፍ፣ ከሐር፣ ከሐር ተረፈ ምርት፣ ወዘተ የተሰሩና በአንገት ወይም በትከሻ ላይ የሚለበሱ ስካርቮች፣ ከላይ ተለባሾች እና መሰል ነገሮች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመኑ ጨርቆች የተሰሩ የስፖርት ሱሪዎች እና ጃኬቶች | | | | | | | | | | |
| ጨርቃጨርቅና አልባሳት | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመነ ጥጥ የተሰራ ሱሪ፣ ቁምጣ፣ ቱታ | | | | | | | | | | |

| iii. የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ (በአመታት) | | |
| | | | አጭር (1 — 3) | መካከለኛ (4 — 7) | ረጅም (8 — 10) |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | የጫማ ምርቶች | ቆዳ ጫማዎች (የቆዳ የተለመደ ጫማ እና የቅንጦት ጫማ) | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | የጫማ ምርቶች | ሌሎች ጫማዎች (የሴቶች ጫማ ፣ የቆዳ ያልሆነ ጫማ ፣ የስፖርት | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | የጫማ ምርቶች | ሌሎች የጎማ ወይም የፕላስቲክ ጫማዎች | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | የቆዳ እቃዎች | የቆዳ እቃዎች | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | የቆዳ እቃዎች | ሴንቴቲክና ከጨርቅ የተሰሩ እቃዎች | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | የጫማ ምርቶች | የላይኛው ጫማ | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | አክሰሰሪዎች (መለዋወጫዎች) | የጫማ ሶል፣ ላስት (ፎርም) እና ሞልድ | | | |
| የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | አክሰሰሪዎች (መለዋወጫዎች) | ሌሎች አክሰሰሪዎች እና ኮምፖነንቶች | | | |

| iv. የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ (በአመታት) | | | | | | | | | |
| | | | አጭር (1 — 3) | | | መካከለኛ (4 — 7) | | | | ረጅም (8 — 10) | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ደረቅና ፈሳሽ ሳሙና | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ቀለምና ቫርኒሽ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | የንፅህና እቃ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ሶልቨንትና ማቅጠኛዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | መሰረታዊ ኬሚካል | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ማጣበቂያና ሌሎች የኮንስትራክሽን ኬሚካሎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ሌሎች የፕላስቲክ ዕቃዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የፕላስቲክ ዝርጎችች፣ ሴሉላር ያልሆኑ እና ያልጠናከሩ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | የፕላስቲክ ቱቦዎች እና ፊቲንጎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች ፕላስቲክ ዝርጎች፣ጥፍጣፎች ወዘተ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ፖሊአስቴል | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የቮልካናይዝድ ረበር/ጎማ ዕቃዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ደረቅና ፈሳሽ ሳሙና | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ቀለምና ቫርኒሽ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | የንፅህና እቃ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ሶልቨንትና ማቅጠኛዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | መሰረታዊ ኬሚካል | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ኬሚካል | ማጣበቂያና ሌሎች የኮንስትራክሽን ኬሚካሎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የፕላስቲክ ዕቃዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የፕላስቲክ ዝርጎችች፣ ሴሉላር ያልሆኑ እና ያልጠናከሩ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | የፕላስቲክ ቱቦዎች እና ፊቲንጎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች ፕላስቲክ ዝርጎች፣ጥፍጣፎች ወዘተ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ፖሊአስቴል | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የቮልካናይዝድ ረበር/ጎማ ዕቃዎች | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ፎም | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | የመኪና ጎማና ጥርሱ የተቀየረ ጎማ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ብዕር/እስክሪቢቶ | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | ፖሊፕሮፕሊን ከረጢት | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፕላስቲክና ጎማ | የፕላስቲክ ፊልም ማሸጊያዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | እንጨትና የእንጨት ዉጤቶች | መክደኛና መያዣዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | እንጨትና የእንጨት ዉጤቶች | የእንጨት ዉጤቶችና ክፍሎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፐልፕና ወረቀት | የካርቶን ማሸጊያዎች | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፐልፕና ወረቀት | የሴቶች ንፅህና መጠበቂያዎች፣ዳፐርና ፊት መጥረጊያ/ ወይፐር | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | ፐልፕና ወረቀት | ፐልፕና ወረቀት | | | | | | | | | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት | መስታዎት | ብርጭቆና ጠርሞሶች | | | | | | | | | | |

## v. ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ ቅድሚያ የተሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ (በአመታት) አጭር (1 — 3) | መካከለኛ (4 — 7) | ረጅም (8 — 10) |
|---|---|---|---|---|---|
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | ተገጣጣሚ የህንፃ መስሪያዎች እና ክፍሎቻቸው፣ ከብረት ወይም ዐረብ ብረት የተሰሩ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | የአሉሚኒየም ወፍራምና ቀጭን ዘንጎች | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | በጠፍጣፋው የተዳመጡ የብረት ወይም አሎይ ያልሆኑ የአረብ ብረት ውጤቶች፣ ወርዳቸው 600 ሚ.ሜ ወይም ከዚህ የበለጠ፣ የለበሱ፣ የተነከሩ ወይም የተቀቡ፣ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | በጠፍጣፋው የተዳመጡ የብረት ወይም አሎይ ያልሆኑ የዓረብ ብረት ውጤቶች፣ ወርዳቸው ከ600 ሚ.ሜ ያነሰ፣ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | ማጠራቀሚያዎች፣ ጋኖች፣ ገንዳዎች እና ለማናቸውም ነገር የሚሆኑ መያዣዎች /ከአምቅ ወይም ከፈሳሽ ጋዝ መያዣዎች ሌላ/፣ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | ጥቅጥቅ ወንፊት /ክብ ስራዎች ጭምር/፣ ፍርግርግ፣ ለመረብ እና ለአጥር የሚሆኑ፣ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት ሽቦ የተሠሩ፤ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠራ ሰፋፊ ቀዳዳ ያለው ዝርግ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ብረትና ዐረብ ብረት | ሌሎች ቱቦዎች ቧንቧዎች እና ውስጠ ክፍት ፕሮፋይልስ/ለምሣሌ፣ የተያያዙ ወይም የተበየዱ፣ በሪቬት የተያያዙ ወይም በተመሣሣይ ሁኔታ የተያያዙ/፣ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሰሩ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ተሽከርካሪ | የአይሮፕላን አካላት | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ተሽከርካሪ | የባለሞተር ተሽከርካሪ አካላት | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ተሽከርካሪ | ባለሞተር ተሽከርካሪ | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ሴንትሪፌጋል ፓምፖች | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የኤሌክትሪክ ሰሌዳዎች/ቦርዶች | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጄኔሬተር | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ለኢንጂን የኤሌክትሪክ እሳት መስጫ/ማስነሻ መሳሪያዎች | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ፓምፖችና ኮምፕረሰሮች | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ኢንሱሌትድ/የተለበጡ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች/ኬብሎች | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ማሽኖችና ክፍሎቻቸው | | | |
| ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የምግብና መጠጥ ማሽነሪዎች | | | |